# <u>ማየት የማይችል አእምሮ ሃገር ያጠፋል ፤በዕውነተኛ ፍልስፍና የማይመራ አገዛዝ ህብረተስብን ይበታትናል</u> !!

***መግቢያ***

**አንባቢዎች የጽሁፋን አርዕስት ወዲያውኑ ሲመለከቱ ከመቼ ጀምሮ ነው አእምሮ ማየት የጀመረው ፤ ዐይን ብቻ ነው ማየት የሚችለው ፣ ስለሆነም በዐይን የታየው ወደ አእምሮ ውስጥ በመተላለፍ አንድን ነገር መገንዘብና ትንታኔ መስጠት ይቻላል ብለው ተገቢ ጥያቄና መልስ ይሰጡ ይሆናል። መልስ የሚሰጡም ብዙ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የግሪክ ፈላስፎች እንደሚያስተምሩን አእምሮ ማየት ካልቻለ ዐይን ማየት አይችልም ይሉናል። የአእምሮ የማየት ኃይል ብቻ ሳይሆን ፣ አእምሮ ራሱ በትክክለኛ ዕውቀት ካልታነፀ ሀቀን ከውሸት መለየት እንደማይቻል ያስተምሩናል። ይህ በሰፈነበት ዓለም ደግሞ ጥቂት ሰዎች አገርን ለማመሳቀልና ህብረተሰብን ለማውደም ይቀላቸዋል።**

**ዛሬ በተለይም አእምሮ በተለያየ ኢንፎርሜሽኖች በየሰዓቱ በሚደበደብበት ዓለም ውስጥ ፣ ሀቁን ከውሸት መለየትና ማን ነው ትክክለኛው ብሎ ፍርድ ለመስጠት በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ግራ ተጋበተው ይገኛሉ። ተማርኩ የሚለው እንኳ ሳይቀር መወናበድ ውስጥ የገባበት ወቅት ነው። የዜና ማሰራጫዎችን የሚቆጣጠሩና በገንዘብ የናጠጡ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ሰዎች ዓለምንና የሰውን ልጅ አኗኗር በፈለጉት መልክ ለመቅረጽና ህዝብን ለመንዳት ይፈልጋሉ። የቴክኖሎጂ ምጥቀት ከፍተኛ በሆነበት ዓለም ውስጥና ብዙ ነገሮች እየተሸብረቀረቁ ለተራ ህዝብ በሚቀርቡበት ቦታ ነገሮችን ጠጋ ብሎ ለማይመረምር ከነዚህ ኃይሎች በሚወረወሩት ኢንፎርሜሽኖች በመማረክና ትክክልኛ ናቸው ብሎ በመቀበል የነሱ የጥፋት ሰለባ ይሆናል። እነሱ እጃቸውን አውጥተው ሲጮሁ ተራውም ህዝብ ሆነ ከነዚህ ጋር በገንዘብም ሆነ በስልጣን ከደለቡ ሰዎች ጋር የተቆላለፈው ወይንም ደግሞ የነሱን የጥፋት ጩኸት በመስማት ብቻ የጥቅም ተካፋይ እየመሰለው ከዳር ሆኖ የሚያጨበጭበው አንድ ላይ ሆነው ሆ በማለት ሁሉም አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ለጥፋት ምክንያት ይሆናሉ። እጅግ የነቃ ሰው ካልሆነ በስተቀር ለመሆኑ የአቶም ቦምብም ሆነ ወይም የባዮሎጂና የኬሚካል መሳሪያዎች መስራት ለምን አስፈለገ ብሎ የሚጠይቅ ብዙም አይደለም። ቢጠይቅ እንኳ በነገሩ አይገፋበትም። በሌላ በኩል ደግሞ እንደዚህ ዐይነቱን መሳሪያዎች መስራት የሚፈቀድላቸው ጥቂት አገሮች ናቸው ፤ የተፈጥሮ መብታቸውም ነው ብሎ የተቀበለና ሌላውን እንደ አክራሪ አድርጎ የሚወስድና ተገቢ ያልሆነ ፍርድ የሚሰጥ ጥቂት እንዳይደለ መገመት ይቻላል።**

**ወደ ሀይማኖትም ስንመጣ የሰው ልጅ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የወደቀ ይመስላል።በተለይም በጥቂት አክራሪ የሀይማኖት መሪዎች በሚወረወሩ አነጋገሮች የሚማረኩ ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች የመሪዎቻቸውን የተደበቀ ዓላማ ባለመገንዘብ በእግዚአብሄር አምሳያ የተፈጠረውን ሌላ ሰው ለማጥፋት ግብግብ ይላሉ። አንድኛው የሀይማኖት መሪ የሱ መመሪያ ብቻ ትክክል ነው ብሎ በማመን ሌላው እንዲቀበል በማድረግ በህዝቦች ዘንድ አለመተማመን እንዲፈጠር ያደርጋል። በሌላ ወገን ደግሞ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን መፍታትና አገራቸውን ማስተዳደር በማይችሉበት አገዛዞች ውስጥ አፍጠው አግጠው ከሚታዩት ለሰው ልጅ መኖር ከሚያስፈልጉት የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ጥያቄዎች ይልቅ የሀይማኖት ጥያቄዎች አጉልተው ስለሚታዩ ህብረተሰቦች ተረጋግተው መኖር ያቅታቸዋል። የገዢ መደቦችም የሀይማኖት ጥያቄ እየቀደመ ሲመጣ ለሱ የሚሆን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ጥያቄውን ያነሳውን አክራሪ ነው በማለት የማያስፈልግ ግብግብ ውስጥ በመግባት የተለኮሰው እሳት እንዲቀጣጠልና ህዝቡን እንዲያዳርስ ምክንያት ይሆናሉ። ይህንን በሚመለከት በተለይም የምዕራብ መንግስታት ያላቸውን የኢንፎርሜሽን ፣ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የሚሊታሪ ኃይል በመጠቀም በሶስተኛው ዓለም አገሮች ፣ በተለይም በአህጉራችን ምድር ጦርነት እንዲቀሰቀስና እኛ በዘለዓለማዊ ትርምስ ውስጥ እንድንኖር ያደርጋሉ። የሱማሌንና የኢትዮጵያን ጦርነት እንመልከት!!**

ወደ ፖለቲካ ትንተናና ወደ ኢኮኖሚ ዕውቀትም ስንመጣ ለምሳሌ ኤክስፐርት ነን በሚሉት በየሬዲዮኑና በየቴሌቪዥኑ የሚሰጠውን ትንተና ስንሰማ በተለይም ነገሮችን ጠጋ ብሎ ለመረዳት የማይችል አንድ ዐይነት ውዥንብር ውስጥ ይወድቃል። ይህንን በምሳሌ ማሳየት ይቻላል። ከአምስት ወር ጀምሮ በአሜሪካን አገር የሚካሄደውን የፕሬዚደንት ፕሪማሪ ውድድር ላይ የሚሰነዘረውን መወነጃጀል ለሰማ አስቂኝ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በተለይም ባራክ ኦባማ አሸናፊ ሆኖ እንዳይወጣ ከተወዳዳሪው ከወይዘሮ ሂለሪም ሆነ አክራሪ ከሆኑት የሪፓብሊካን ክንፎች የሚሰነዘረው ክስ ፖለቲካ የቱን ያህል ማታለያና ስልጣን ላይ ብቻ ቁጥጥ ለማለት ጥቂት ኃይሎች እንደሚጠቀሙበት መገንዘብ ይቻላል። ባራካ ኦባማ ከመንፈስ አባቱ ጋር ከሬበረንድ ራይት ጋር የነበረውን ግኑኝነት አስመልክቶ የደረሰበት ክስና ዘመቻ በአንዳንድ ቦታዎች አሸናፊ ሆኖ እንዳይወጣ አግዶታል። ሜኬይንና ሂለሪ እነሱ ብቻ አገር ወዳዶች(patriots)፣ ባራክ ደግሞ ስልጣን ለመውጣትና አገርን ለመምራት ብቃት የለውም የሚለው በተለይም ሰራተኛውን የአሜሪካ ህዝብ እያታለለ ነው። ለብዙው የአሜሪካ ህዝብና ለአክራሪው የሪፓብሊካን ክንፍ አንድን አገር በጦር ሄዶ መደብደብና መውረር እንደ ሃገር ወዳድነትና ጀግነነት ነው የሚቆጠረው። በአካባቢው የሚታየው የመግደልና የመገዳደል ሁኔታና ከቁጥጥር መውጣት፣ የኢኮኖሚው መድቀቅና የሰራተኛ አጥ ቁጥር በየጊዜው እያደገ መምጣት፣ ህብረተሰብአዊ ግኑኝነቶች መናጋትና የባህል ሁኔታ መፈረካከስ፣ ብዙውን የአሜሪካ ህዝብ የሚያሳስበው አይመስልም። ይህንን የተገነዘቡት የኮንሰርቫቲቮች አፈቀላጤ የዜና ማሰራጫዎች ህብረተሰቡን ከዕውነተኛው ችግር ለማላቀቅና ወደ ሌላ ነገሮች ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ችግሩ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ እንዲሸጋገር እያደረጉ ነው። ይህንን በሚመለከትና የዕውነተኛ አገር ወዳድነት ትርጉም ባንዲራን በመልበስ ሊገለጽ እንደማይችል ህዝቡን ለማስረዳት ባራክ ኦባማ የማያደርገው ጥረት የለም። በተጨማሪም ፊሲካል ኮንሰርቫቲዝም የሚለውን በቀኝ ሪፓብሊካኖች የሚወረወረውን አባባል ለሰማና ጥያቄ ለማቅረብ የማይፈልግ አባባሉ ትክክል ነው ብሎ በመውሰድ የተሳሳተ ድምደማ ውስጥ ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ የጦር መሳሪያ ለማምረት የሚወጣው ገንዘብና ጦርነትን ለማካሄድ የሚፈሰው ገንዘብ ለምን እንደሚባክንና መባከንስ እንዳለበት ለመጠየቅ የሚቃጣ የለም። በኮንሰርቫቲቮች አባባል ፊስካል ኮንሰርቫቲዝም ማለት ህብረተሰቡን ለመያዝና ለማገዝ የሚወጡት የማህበራዊና የባህል ድጎማዎች መቀነስ ወይም መቅረት አለባቸው ማለት ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ትርጉም የለውም። ኮንሰርቫቲቮች የህዝቡን አስተሳሰብ ለማዛነፍና ዕውነቱን ከዕውሸት እንዳይለይ የሚጠቀሙበት መሳሪያ በዚህ ላይ ብቻ የሚያቆም አይደለም። ማሰወረድን እንቃወማለን(pro life)እያሉ የሚነዙት ልፈፋ በእርግጥም ለሰው ልጅ ርህራሄ ያላቸው ያስመስላቸዋል። እንደምናየው ከሆነ ግን በአንድ በኩል ይህንን መፈክር እያስተጋቡ በሌላ በኩል ደግሞ ከራሳቸው ድንበር አልፈው ኢራክና አፍጋኒስታን በህይወት ላይ ያሉና አዲስ ዕድል ይጠብቀናል ብለው የሚጓጉትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ህጻናት ካለምንም ርህራሄ በአውሮፕላን ሲደበድቡ እናያለን። ይህንን ኮላትራል ዳሜጅ እያሉ ነገሩን አቃለው በማሳየት አብዛኛው ህዝብ የነገሮችን ሂደትና ድርጊት እንዳይረዳ የማያደርጉት ሙከራ ይህ ነው አይባልም። በተጨማሪም በሃገራቸው ውስጥ ተወልደው ብዙ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ህጻናትንና ወጣቶችን ጤናማ ዜጋ እንዲሆኑ ከመንግስት በኩል መደረግ ያለበት እርምጃ በፍጹም አጥጋቢ አይደለም። ታዲያ በህይወት ያሉትን በሚገባ ሳይንከባከቡ እንዴት ገና ላልተወለደው ህጻን ጠበቃ እንቆማለን ሊሉ ይችላሉ? ኮንሰርቫቲዝም የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ እንመልከት።በመሰረቱ ኮንሰርቫቲዝም ማለት ወግ-አጥባቂ ማለት ነው። ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣን ባህል መጠበቅ ማለት ነው። ቤተሰብን መንከባከብ ማለት ነው። በኮንሰርቫቲቮች አመለካከት በባልና በሚሰት መሀከል ግልጽ የሆነ የሥራ ክፍፍል አለ። ሚስት ቤትን የምንትከባከብ፣ ልጅን የምታሳድግ ነች። በሃይማኖትም እንደዚሁ የክርስቲያንን ሃይማኖት እሴት(core values) መጠበቅና ለደካማው ጠበቃ መሆን ነው። በሌላ አነጋገር ወንድማማችነትንና ሰብአዊነትን አጥብቆ በማንሳት በአንፃሩ ደግሞ  ጦርነትን መቃወም ነው። የዘመኑ የኮንሰርቫቲቭ ፓርቲዎች ከአሜሪካ እስከ አውሮፓ ድረስ ያሉት ከላይ የተጠቀሱትን መሰረተ-ሃሳቦች የሚጻረሩ ናቸው። ከውስጥ የሀብታሞችን ጥቅም ማስጠበቅና በዚህም በዚያም ብለው ሀብት ከሰራተኛው የህብረተሰብ ክፍል ወደ ሀብታሙ የሚሸጋሸግበትን መንገድ የሚያዘጋጁ ናቸው። ከትምህርት ዕድል እስከ ማህበራዊ ነክ ጥቅሞች ድረስ ሰፊው ህዝብ ጥቅም እንዳያገኝ ተንኮል የሚሸርቡ ናቸው። የሰራተኛው ልጅ የዩኒቨርሲቲ ዕድል እንዳያገኝ ከመጀመሪያወኑ መንገዱን ሁሉ የሚዘጉ ናቸው። የሎቢስቶችን ጥቅም በማሰጠበቅ ወደ ውጭም ልዩ ልዩ ምክንያቶችን እየፈለጉ ለጦርነት የሚዘጋጁ ናቸው።

ይህ ከላይ የቀረበውን የኮንሰርቫቲቮችም ሆነ ጠቅላላው የዜና ማሰራጫ በሰው አስተሳሰብ ላይ ያለውን ተጽዕኖና አመለካከትን ማዛነፍ ራሴ ካጋጠመኝ ልምድ አንዳንድ ነገር ብል የበለጠ ነገሩን ግልጽ ያደርገዋል። የምኖርበት ከተማ ለጉብኝት የመጡ ጠና ያሉ

ሁለት ወንዶችና ሴቶች አሜሪካኖች በአገጣሚ አገናኛለሁ። ስለከተማው ውበት ስናወራ ስለወንጀል ጉዳይ ጠየቁኝ። በዕውነቱ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እስከዚህም ድረስ በግልጽ የሚታይ ነገር እንደሌለና ሽማግሌውም ሆነ ወጣቱ ተዝናንቶ እንደሚሄድ አስረዳኋቸው። ለምን እንደዚህ እንደሆነም ገለጽኩላቸው። እኔ ደግሞ በበኩሌ ሰዎቹ ከቺካጎ የመጡ ስለነበር እዚያ ስላለው ወንጀል እንዲያስረዱኝ ጠየቅኋቸው። ቺካጎ መኖር ለህይወት አደገኛ እንደሆነና ብዙም ሰው ጠብንጃ እንዳለው አስረዱኝ። ምክንያቱ ምንድነው ብዬ ስጠይቃቸው ብዙው ወጣት መስራት ስለማይፈልግ ወንጀል ከሰራ እስር ቤት ይወረወራል። እዚያ ሆኖ ከመንግስት ሁሉን ነገር ያገኛል የሚል መልስ  ሰጡኝ። በእነሱ ዕምነት ለወንጀሉ ዋና ምክንያት ወጣቱ ራሱ ተጠያቂ እንጂ ሰርዓቱ የፈጠረው ሁኔታ አይደለም። ይህ የተሳሳተ ግምት እንደሆነና ከቤተሰብ መናጋትና ወላጆችም ባላቸው ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ሁኔታ ለልጆቻቸው አስፈላጊውን እንክብካቤ ሊያደርጉላቸው አይችሉም።በዚህ ላይ ብዙ ልጆች በእናቶቻቸው ብቻ ካለአባት ያድጋሉ። የቤተሰብ መፈራረስ ለዚህ ሁኔታ ምክንያት ነው። በተጨማሪም በየቦታው ያለው የሎካል አስተዳደር ልጆች ከትምህርት ገበታቸው በኋላ ወደ አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ የግዴታ እንደ ስፖርትና ሙዚቃ የሚለማመዱበትና የሚማሩበት ቦታ እያዘጋጀ ማቅረብ አለበት። አንድ የሎካል አስተዳደር ያለበት ኃላፊነት በየአካባቢዎቹ ችግሮች እንዳይፈጠሩ አስፈላጊውን የህብረተሰብና የባህል እንክብካቤ ማድረግ አለበት። መንግስትና የሎካል አስተዳዳሪዎች ህብረተሰብአዊ ኃላፊነታቸውን በማይወጡበት ቦታ የግዴታ የተወሰነው ወጣት ወደሚሆነው ወደማይሆነው ይሰማራል። ቀስ በቀስም ይህ ሁኔታ እየተለመደ ሲሄድ መንግስት ሊፈታ የሚቃጣው በኃይል ብቻ ይሆናል ብዬ አስረዳኋቸው። ነገሩ የገባቸው መሰለኝ። በመቀጠልም ስለ ምርጫው አነሳሁባቸው። ባራክ ኦባማ የሚባል ሰው መጥቶ ያሰቸግራችኋል ብዬ ትንሽ ለመቀለድ ሞከርኩ።  አየህ ሂለሪም ሆነ ባራክ ኦባማ ሶሻሊስቶች ስለሆኑ ስልጣን ቢይዙ ገንዘብ መበተን ይጀምራሉ አሉኝ። ካደመጥኩኝ በኋላ ፣ ይህ ሊሆን እንደማይችል ነገርኳቸው። በመጀመሪያ ሶሻሊስቶች ናቸው የሚለው አባባል ኮንሰርቫቲቮች ህዝብን ለማስፈራራት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው። ከዚህ በተረፈ ማንኛውም ፓርቲ ሆነ ፕሬዚደንት የተወሰነ ህግን ተከትሎ እንደሚሰራናና ባራክም ሆነ ሂለሪ ቢመረጡ በመጀመሪያ የሚሰጡት ቅድሚያ እንዳለና ይህ ደግሞ አስፈላጊ እንደሆነ አስረዳኋቸው። በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ ኢኮኖሚ እጅግ ተዳክሞ ይገኛል። መንግስት አንድ እርምጃ ካልወሰደ ችግሩ እየተባባሰና ህብረተሰብአዊ መናጋት ተፈጥሮ የወንጀለኛ ቁጥርም እንደሚጨምር አብራራሁላቸው። ያልጠበቁትን ስለነገርኳቸው ትምህርት እንደተማሩ ነገሩኝ። እንግዲህ ሃገራችሁ ስትመለሱ ባራክን ወይንም ሂለሪን እንደምትመርጡ ተስፋ አደርጋለሁ ብዬ ተሰነባበትን። ከዚህች መረዳት የምንችለው አንድ ህብረተሰብ በተሳሳተ ኢንፎርሜሽን እንዴት እንደሚነዳና ወዳልሆነ አቅጣጫ እንደሚያመራ ነው። በተለይም የተወሰኑ ፓርቲዎች እዚያው በዚያው በሚሽከረከሩበትና(recycle) የተወሰኑ አመለካከቶች በሚደጋገሙበት ህብረተሰብ ውስጥ ህዝቡ መሪዎች የሚያወሩት ሁሉ ዕውነት ይመስለዋል።

ነገሩን ለመዝጋት ወደ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ላምራ። እንዳጋጣሚ ከአንድ ጥቁር አሜሪካዊ መኮንን ጋር እንገናኛለን። አንድ ቦታ ሁኜ ጋዜጣ አነብ ነበር። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ከየት ነው የመጣኸው ብሎ ጠየቀኝ። የመጣሁበትን ስነግረው ይገርምሃል ኢትዮጵያውያን ጓደኞች አሉኝ አለኝ። ትንሽ እንደመጠርጠር ካልኩ በኋላ ሳላስበው ወደ ኢራቅ ጦርነት ውስጥ ገባሁ። እናንተ አሜሪካኖች ዓለምን ለመቆጣጠር የማትሰሩት ወንጀል የለም። ማንም መብት ሳይሰጣችሁ አንድ ሃገርና አንድ ህብረተሰብ ትደበድባላችሁ ፤ታመሰቃቅላላችሁ አልኩት። ሊያስረዳኝ ሞከረ። ስማ አለኝ። እያንዳንዱ ሰውና ሃገር ራሱን መከላከል አለበት አለኝ። እኔም በመመለስ በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ሃገር በሌላ ሲጣቃ ብቻ የዚያን ጊዜ መከላከል ይችላል። እናንተ የወሰዳችሁት እርምጃ ግን መከላከል ሳይሆን ማጥቃት ነው። የሰው ሃገር መውረር የእግር ጉዞ አድርጋችሁ አሁን የማትወጡበት አዘቅት ውስጥ ገብታችኋል። እናንተ የዲሞክራሲ ባህርይ ቢኖራችሁና ደግሞም ወደፊት የዘይት መቋረጥ ይኖራል ብላችሁ ብትገምቱ በውይይት መፍታት ትችሉ ነበር። የናንተ ዓላማ ግን ይህ አይደለም። መጀመሪያ አያቶላ ሁሜኒን ቀስ ብላችሁ ከፓሪስ እንዲመለስ አደረጋችሁ። ቀጥሎም ሳዳምን እስከ አፍጢሙ ድረስ አስታጠቃችሁት። በሁለቱ ሃገሮች መሀከል ጦርነት እንዲነሳ አሻጥር ሰራችሁ። በኋላ ሳዳም እየተጠናከረ ሲመጣ አሁን እሱን ሌላ ወጥመድ ውስጥ የምትከቱበትን መንገድ ወደ ማዘጋጀት አመራችሁ። ኩዌትን እንዲወር ፈቀዳችሁለት አልኩት። ይህ ሁሉ ውሸት ነው አለኝ።ስማ ሌባና ገዳይ ሰርቄያለሁ ወይም ገድያለሁ አይሉም። የናንተም ችግር ይህ ነው። ይህንን ሁሉ ከዘረዘርክልኝ በኋላ ከጦርነቱ እንዴት እንደምንወጣ ንገረኝ አለ። በመጀመሪያ ክላውዘቪትዝ የተባለው የጦር ፈላስፋ እንዳለው ፣ የጦር ዋናው ስትራቴጂ በምንም ዐይነት ጦርነት እንዳይጀመር መጣር ነው። አንድ ጊዜ ጦርነት ውስጥ ከተገባ በኋላ ለመውጣት ይከብዳል።እናንተ የጀመራችሁት ስለሆነ ዝምብላችሁ ብትወጡ የዲፕሎማቲክና የፖለቲካ

ሸንፈት ያጋጥማችኋል። የናንተ ዋናው ችግር ግን ይህ አይደለም ፤ ፍልስፍናችሁ በሙሉ በዚህ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ጦርነትን ለመቀስቀስ የማታደርጉት ሙከራ የለም። ጠቅላላው የአሜሪካ ኤሊት በዚህ በተበላሸ ፍልስፍና ያምናል። አሜሪካ የዓለምን ህዝብ ዕድል ሁሉ ወሳኝ አድርጋችሁ ተቀብላችኋል። ለምሳሌ ረምስፌልድ የመከላከያ ሚኒስቴራችሁ ያለውን ስማ። አውሮፓውያኖች በኢማኑኤል ካንት ፍልስፍና ነው የሚመሩት ፤ እኛ ደግሞ በሆበስ ፍልስፍና ነው የምንመራው ብሏል። በዚህ የተበላሸ ፍልስፍና እስከምታምኑ ድረስና የሌላውን ሃገር የመኖር መብት እስካላወቃችሁ ድረስ ህልማችሁ ሁሉ ጦርነት ነው። ስለዚህም ጠቅላላው የአስተሳሰብ ስልታችሁ( method of thought) መቀየር አለበት። ይህ የተበላሸ አስተሳሰባችሁ ለኛም ተርፎን መኖሪያ አሳጥቶናል። በተለይም የሦስተኛውን ዓለም ሃገሮች ቴክኖክራቶና ቢሮክራቶች በዚህ በተበላሸ ፍልስፍና በማሰልጠን ህዝቦች ሊሰሩ የሚችሉትን ታሪካዊ ስራ እንዳይሰሩ ታግደዋል። የናንተም መውደቂያ ሩቅ አይደለም። ብዙ ሰዓት ካወራን በኋላ ነገሮች እየከነከኑት መጡ። በውሸት ዓለም ውስጥ እንደሚኖር እየተገነዘበ የመጣ መሰለኝ። መሄድ ስለነበረብኝ ፣ it is nice to meet you, it was a very intetresting discussion !! ብሎኝ ተለያየን። ከኦፊሰሩ አስተሳሰብና አወራር እንደተገነዘብኩት ነገሮችን ሁሉ ገልብጦ ነው የሚረዳው። ሌሎች ሃገሮች ታሪክ እንደነበራቸውና እያንዳንዱ ህብረተሰብም የራሱን ዕድል በራሱ መወሰንና ራሱን በፈለገው መልክ ማደራጀት ተፈጥሮአዊ መብቱ እንደሆነ በፍጹም የተረዳ አይመስልም። የዓለምን ህብረተሰብ ዕድል ከአሜሪካ ፖለቲካ አንፃር(from the American perspective) ነው የሚመለከተው። በዚህ መልክ እሱ ብቻ ሳይሆን በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች በውሸት  ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩና ራሳቸውን ሳይጠይቁ የጥቂት ግለሰቦችም ሆነ የአንድ ገዢ መደብ ሰለባ እንደሚሆኑ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ዐይነቱ የተሳሳተ ፍልስፍናና የብዙ ህብረተሰቦች መወናበድ ሃገሮችን ወደ ጦርነት ውስጥ እየከተተና ለታሪክና ለባህል ውድመት ምክንያት እየሆነ ነው። ወደ ሃገራችንም ስንመጣ በሌላ መልክ የሚካሄደው ጦርነትና የሚፈጠረው ችግር የሰውን ልጅ የታሪክ ሰሪነት ለመገንዘብ ያለመቻልና የአንድን ህብረተሰብ ዕድል ጦርነት አድረጎ ከመውሰድ ጋር የተያያዘ አርቆ ካለመሰብ የሚመነጭ አጉል ድርጊት ነው። የብዙዎቻችንም ፖለቲካ ከዚህ ታሪክን ከሚያሰራ ሳይሆን ህብረተሰብን ከሚያወድም የአሜሪካን የፖለቲካ ፍልስፍና ጋር የተቆራኘ ነው። በተለይም ኢህኤዴግን የሚደግፉ ካድሬዎች ፓልቶክ ውስጥ ገብቶ ላዳመጠ ይህንን ዐይነቱን የዐመጽ ፖለቲካ ነው የሚያራምዱት። ይህ በሽታ ሌሎች ፓልቶክዎች ውስጥም ሲንሸራሸርና መስመር በመለየትና ባለመየት መሀከል ወይም ደግሞ የወዳጅ ጠላት ፖለቲካ ዐይነት ፣ የእኔን ሃሳብ ያልተከተለ መደቆስ አለበት ወደ ሚለው እያደላ የመጣ ነው። ለጥያቄና ሰፋ ላለ አስተሳሰብ በፍጹም ዕድል የማይሰጥ ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድል በጥቂት መሬዎች ነን በሚሉ ግለሰቦች ዘንድ የሚወሰን የሚያስመስል ውይይት ነው የሚሰማው።

ወደ አገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ስንመጣ አገዛዙ አገሪቱን ረግጦ ለመግዛትና ህዝቡን ለዝንተዓለም አድኽይቶ ለማስቀረት የሚጠቀምበት መሳሪያ እንደምዕራቡ ዓለም የተወሳሰበና በርዕዮተ-ዓለም የተሸፈነ አይደለም። ህዝብን ረግጦ ለመግዛት የሚችልበት መሳሪያ ኃይልን ብቻ በመጠቀም እንጂ አሳሳች ኢንፎርሜሽኖችን በማሰራጨት ህዝብን ለማታለል የሚችልበት መሳሪያ በፍጹም የለውም። አፍጠው አግጠው የሚታዩትን ችግሮች መንግስት የሉም ብሎ ሊዋሽ የሚችልበት የማታለያ ወይም የማካሳሺያ መሳሪያ ስሌለለውና ስልጣን በተፈጥሮ ያገኘ ስለሚሰመስለው በመጨቆኛ መሳሪዎች ብቻ እየተጠቀመ ህዝብን ረግጦ ይገዛል። መንግስትን የህዝብ ችግር መፍቻ መሳሪያ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ ማምለኪያና የራሱ ብቻ አደርጎ በመቁጠር ፖሊሲውን የሚቃወሙትን ሁሉ እንደ ጠላት ይመለከታቸዋል። ይህ አመለካከት ደግሞ የግዴታ ከህብረተሰብአችን የማቴሪያልዊ ዕድገት ዝቅተኝነትና የአስተሳሰብ አለመዳበርና ከውጭ ተቆራርጦ የገባው የተሳሳተ „ዕውቀት“ በጥቂት ሰዎች አካባቢ ብቻ ከመሸከርከር ጋር የተያያዘ ነው። የሚያሳዝነው ግን የአገዛዙ እንደዚህ የአእምሮ መታወር ሳይሆን በየፓል ቶኩ ውስጥ የዶክተርንትን ማዕረግ ይዘው ይዘዙኝ ልቀቁኝ የሚሉትንና እነሱ ከሚሰጡት ትንተና ውጭ ሌላ የተሻለ የሌለ የሚመስላቸውና ወጣቱን የሚያታልሉትን የቱን ያህል አገር ለማውደም እንደተነሱ እንደማይታያቸውና ጥያቄ ማቅረብ እንደሚሳናቸው ነው። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የተማሩት ትምህርት ኢሰብአዊ የሚያደርግና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነትን እንዲዘነጋ የሚያደርግ ነው ወይ ? ወይስ ሌላ ምክንያት ሊኖረው ይችላል? የሚለውን አንስቶ በጭንቅላት ውስጥ ማውጠንጠን አስፈላጊ ይመስለኛል።

ያም ሆነ ይህ የምዕራቡ ፖለቲከኛም ሀነ የሃገራችን ፖለቲከኛ ባይ የመጨረሻ መጨረሻ ሃገራቸውን ችግር ውስጥ ይከቱታል። የሃገራችን የመበታተን ሁኔታ ሊፈጥን ይችላል። የምዕራቡ ፣ በተለይም የአሜሪካው ግን እየተራመሰ ፣ ነጩ በጥቁር ላይ በመነሳት ወይም

ደግሞ የተገላቢጦሽ ዕምነት እያጡ እንደሰው ልጅ ታሪክን እየሰሩ በሰላም እንዳይኖሩ ይሳናቸዋል። ህብረተሰብአዊ ትርምስ የህብረተሰቡ ኖርም በመሆን ሀብታሙ በደሀ ላይ ዘመቻ እያደረገ ተፋጠው ይኖራሉ ማለት ነው።

ይህ ዐይነቱ ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀል በአንድ በኩል እያለ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ጥቂት ምሁሮችና የገዢ መደቦች አንድ ህዝብ ጭንቅላቱን እንዳይከፍት ፣የኑሮን ትርጉም ተረድቶ ጥበባዊ በሆነ መልክ ኑሮውን እያደራጀ እንዳይኖር ለምን ውዥንብር ውስጥ ይከቱታል? ለምንስ በራሱ ላይ ዕምነት እንዲያጣ ያደርጋሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በፍልስፍና መነጽር ለመመርመር እንሞክር። በጸሀፊው ዕምነት መሰረት በማንኛውም ሃገር ይሁን አንድ ህብረተሰብ በአንድ በኩል በጀግንነት ብቻ እየተመካ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በውሸት ፕሮፖጋንዳ እየተታለለ ለረጅም ጊዜ ሊኖር አይችልም። አንድ ህብረተሰብ የገዢ መደቦች በየጊዜው በሚሸርቡት ተንኮል እንዳይመሰቃቀል ከተፈለገ የግዴታ ተንኮላቸውን ማወቅ አለበት። በንቃት መጠባበቅ አለበት። ለዚህ ደግሞ ጭንቅላቱን በየጊዜው ማደስ አለበት። በዚህም ረገድ በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የተደረጉትን ሙከራዎች ጠጋ ብለን እንመልከት።

## <u>የህብረተሰብ ታሪክ ምን ይላል ?</u>

ስለ ሃገራችን የገዢ መደቦች ባህርይና ድርጊት ፣ በተለይም ደግሞ ስለ አሁኑ አገዛዝ ፖለቲካዊ ተግባር በሚወራበት ጊዜ የዲሞክራቲክ አሰራርና በዚህ መርህ ላይ የተመረኮዘን አሰራር ያለመቀበል ችግር እንዳለ ተደርጎ ነው የሚወራው። በተለይም የምዕራቡ ዓለም ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቢያንስ በአፍ ተቀባይነት ባገኘበት ዘመን እንደኛ ባሉ የኋሊት ጉዞ በሚያደርጉ ህብረተሰቦች ውስጥ የሚከሰቱና የተስፋፉ የአስተዳደር በደሎችና ጭቆናዎች ከዲሞክራሲያዊ መብቶች አለመኖርና አለመከበር ጋር ነው የሚያያዙት። በሌላ አነጋገር ፣ ዲሞክራሲያዊ አሰራሮች ከራስ ጋር መዋሀድና የሌላውን ሰው መብት ማክበርና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነትንም መቀበል በመጀመሪያውኑ ጭንቅላትን ከመግራትና ራስን አውቆ የሌላውንም ሰው መብት ከማወቅ ጋር ተያይዞ አይደለም የሚተነተነው። ስለሆነም በአንድ ሃገር ውስጥ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር አለመኖር ፣ የገዢዎች መባለግና በራሳቸው ፈቃድ እየተነሳሱ የራሳቸውን ህግ እንኳ ሳይቀር ጥሶ የህብረተሰቡን መንፈስ የሚረብሽና ተረጋግቶ እንዳይኖር የሚያደርጉ እርምጃዎች መውሰድ ከህብረተሰብአዊ ዕድገት ሂደቶች ፣ የተወሰኑ ባህላዊ አሰራሮችና ልምዶች መስፋፋትና እነዚህ በሌላና በተሸለ መተካት እንዳለባቸው ካለመረዳት ጋር በጥብቅ እንደተያያዙ ሆነው አይደለም የሚቀርቡት። በዚህም ምክንያት በአንድ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አሰራሮች የአንድ አገዛዝ ባህርይ ብቻ ተደርገው የሚወሰዱበት ሁኔታ አለ። በሌላ ወገን ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት የሚነሱ አገዛዞች አንደኛው ቀደም ብሎ ከነበረው የአገዛዝ ስህተት ለመማር ስለማይፈልግ የህብረተሰቡን ችግር በሌላ መልክና ጥልቀት እያሰፋና እያፋጠነ ህብረተሰብአዊ ውዝግቦች ለረጅም ጊዜ መፍትሄ እንዳያገኙና እየተደራረቡ እንዲመጡ በማድረግ አንድ ህዝብ መስራት ያለበትን ታሪካዊ ስራዎች እንዳይሰራ የረጅም ጊዜ በሽታ ጥለው ያልፋሉ። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ለምንድ ነው በተለያየ ወቅት የሚነሱ የገዢ መደቦች ህዝብ እንዲረጋጋ ፣ ታሪክ እንዲሰራ ቀና መንገድ የማይከተሉት ? ለምንስ ከአንድ ስህተት ወደ ሌላ በማምራት ህብረተሰብአቸውን ለጥፋት ይዳርጉታል? ምንስ ጥቅም ያገኛሉ ? ለምንስ ጭንቅላታቸው ይጋረዳል ? የሚሉትን ጥያቄዎች ከታሪክ አንፃር እያነሱ በመጠኑም ቢሆን መወያየት ያስፈልጋል። የአንድ ህብረተሰብ ችግር በተራ ምርጫና እኔ ከሌላው የተሻልኩ ዲሞክራት ነኝ በሚል መፈታት እንደማይቻል ቢያንስ ያለፉት ሀያና ሰላሳ ዐመታት በብዙ የሶስተኛው ዓለም ሃገሮች በዲሞክራሲያዊ ስም የገዢዎች መለዋወጥ የተጠበቀውን ውጤት እንዳላመጣ መማር እንችላለን።

አብዛኛውን ጊዜ ስለ ምዕራቡ ዲሞክራሲና አሰራር እንዲሁም ተቻችሎ መኖር እንደምሳሌ ተደርጎ በሚወሰድበት ጊዜ መነሳትና በየጊዜው መጠናትም ሆነ ለውይይት መቅረብ ያለባቸው መሰረተ ሃሳቦች እንዳሉ በፍጹም ግንዛቤ ውስጥ አይገባም። እንዲያውም አንዳንዶች አልፈው በመሄድ ዲሞክራሲያዊ አሰራርና ተቻችሎ መኖር ለምዕራቡ ዓለም የተሰጠ ቡራኬ እንደሆነና በአፈጣጠራቸውም ዲሞክራቶች እንደሆኑ ተደርጎ በመቀበል የሰው ልጅ በአፈጣጠሩ እኩል እንዳልሆነ የሚቀርብበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በምዕራቡ ዓለም የተከሰቱ እንደ ናፖሊዎንና እንደ ሂትለር የመሳሰሉ አምባገነኖችና ፈሻሽታዊ አገዛዞች ፣ የሰቀነኑ ፀረ-ሰውና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አሰራሮች እንደ ታሪክ ልምድና በተለያየ

መልክ በልዩ ልዩ ሃገሮችም ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግንዛቤ ውስጥ አይገቡም ፤ ወይም ደግሞ በጊዜው በነዚህ አገሮች የተወሰነ የቴክኖሎጂ ዕድገት እየታየ የሌላውን አገር አጥፍተው የመጨረሻ መጨረሻ የራሳቸውን ሃገር የሚያጠፉ አገዛዞች ለምን እንደሚነሱ ጥያቄ አይነሳም። ይህ ማለት በተለያዩ ቦታዎች የተነሱ ፀረ-ዲሞክራሲና ፋሺሽታዊ አገዛዞች በሌሎች ሃገሮችም በሌላ መልክና ጥልቀት ሊከሰቱ እንደሚችሉ ከታሪክ መማር እንችላለን። ይህ ማለት የየሃገሮችን ህብረተሰብ አወቃቀርና የታሪክ ልምድና የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግኑኝነት አካትተን መመልከቱን ትተን ፣ በአጠቃላይ ሲታይ የሰው ልጅ ጭንቅላት ጥፋትንም ሆነ ልማትን የያዘ ነው። አርቆ ማሰብም ሆነ አለማሰብ እንደግለሰቦች የጭንቅላት አወቃቀር ፣አስተዳደግ ፣ የዕውቀት ዐይነትና ሁኔታ ሚዛኑ ወደ አንደኛው ክፍል ያደላል። ይህ በእንደዚህ እንዳለ የአንድ ሰውም ሆነ የአንድ ህብረተሰብ የማሰብ ኃይል ሊዳብርም ሆነ እዚያው ባለህበት ረግቶ ሊቀር የሚችለው በተወለደበት ህብረተሰብ ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፉ የአሰራር ኖርሞች ነው። በሌላ አነጋገር በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በሰፊውና በጥልቀት ማሰብ ፣ የመደማመጥና መከባበር እንደሁም ታታሪነትና ራስን ችሎ ህብረተሰብአዊ ታሪክን መስራት በዚያ ህብረተሰብ ውስጥ በዳበሩ የአሰራር ኖርሞች ነው ሊወሰን የሚችለው። አንድ ህብረተሰብም ወደ ፊት ሊጓዝና እንደህብረተሰብ ሊኖር የሚችለው በሽታውን ሲያውቅ ብቻ ነው። ከበሽታውም ለመላቀቅ አዲስና ፍቱን መፍትሄ ሲያገኝ ብቻ ነው። ዕውነተኛ ታሪክ ተሰራባቸው ፣ ቴክኖሎጂያዊ ምጥቀት ታየባቸው ፣ በዚህም የሰው ልጅ ማንነቱን አውቆ ታሪክን እየሰራ ነፃነቱን ተቀዳጀባቸው የምንላቸውና ምናልባትም አንዳንዶቻችን የምንመኘውን የምዕራቡን ስልጣኔ ዕድገት ስንመረምር ከዚህ ራስን ከማግኘትና የማሰብ ኃይልን በአዲስ ዕውቀት ከማዳበር ጋር እንደተያያዘ ማረጋገጥ ይቻላል። ዕውነተኛና የተስተካከሉ ዕድገቶች የተገኙት ከላይ ወደ ታች በጥቂት የገዢ መደቦች እንደ ፍርፋሪ በሚያስፈልግ ጊዜ ብቻ እየተወረወሩ በመሰጠታቸው አይደለም። ይህንን ሀቅ ለመረዳት በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የተደረጉትን በተለይም ከጭንቅላት ጋር የተያያዙ ትግሎችንና ውጤታቸውን ጠጋ ብለን እንመልከት።

ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አንድ ህብረተሰብ ለምንድነው ዕጣው ጦርነት የሆነው ? ለምንድን ነው የወንድማማች ጦርነት እንደተፈጥሮአዊ ህግ ተደርጎ በመወሰድ ታሪክን ከመስራት ይልቅ አንዱ ሌላውን መግደል እንደ ጀግንነት የሚታይበት ተብሎ ሰፊ ጥናት የተካሄደበት ሃገር ቢኖር በተለያዩ ጎሳዎች ተከፋፍላ በምትኖረው ዛሬ ግሪክ ተብላ በምትጠራው ውስጥ እንደነበር በጥናት የተደረሰበት ነው። የሆሜር የኢልያድና የኦዲዩሲ የኤፒክ ስራዎች የሚያረጋግጡት በዚያን ጊዜ የነበረውን ዝቅተኛ የማሰብ ኃይል ሁኔታ ነው። በሆሜር ኤፒክ መሰረት የትሮይ ንጉስ ልጅ የነበረው ፓሪስ በግሪክ ንጉስ ሴት ልጅ ውበት በመማረክ ሰርቆ ይወስዳታል። ይህ ጠለፋ የግሪክ ንጉስ የሆነውን አጋሜምኖን ያናድደዋል። አጋሜምኖን ሰራዊቱን በማዘጋጀት በአቺል የጦር አዝማችነት በትሮይ ላይ እንዲዘምት ያደርጋል። አስር ዐመት ያህል ጦርነቱ ይካሄዳል። ትሮይ በግሪክ ጦር በመከበቧ ክፉኛ ትደበደባለች። ይሁንና በንጉሱ አጋሜምኖንና በጦር አዝማቹ በአቺል መሀከል በተነሳው አለመግባባት አቺል ወደ ሃገሩ ይመለሳል። ትሮዮች ከዘጠኝ ዐመት ውጊያ በኋላ እስትንፋስ በማግኘት የግሪክን ጦር ወግተው መመለስ ይችላሉ። በኤፒኩ መሰረት ጦርነቱ በተለይም በግንባር ቀደምትነት የተካፈሉትን አዝማቾች ባህርይ ደካማም ሆነ ጠንካራ ጎን ያሳያል። የአቺል ከጦር ግንባር ቀደምትነት ቦታው መመመለስና ጦሩ እንዲሸነፍ ማድረግ የጨቅላነት ባህርይን ያመለክታል። በተጨማሪም በዚህ ትርጉመ-ቢስ ጦርነት የተሰለፉት ወታደሮች ከቤተሰቦቻቸው ወደው እንዳልተለዩ ፣ ግዴታቸውን ማሳየት እንዳለባቸውና ቤተሰባዊ ፍቅርም እንደነባራቸው ኤፒኩ ያመለክታል። የሆሜር ኤልያድ በወንድማማቾች መሀከል የሚካሄድን ፣ በሆነው ባልሆነው የሚነሳን ጦርነት የሚቃውም ነው። ጦርነት ዘግናኝና አንድ ጊዜ ከተጀመረ መረን በመልቀቅ የሰዎችን የተደበቀ መጥፎ ባህርይ አውጥቶ የሚያሳይ መሆኑን ከኤፒኩ መረዳት ይቻላል። አርቆ ማሰብ የማይችለው ክፍል አይሎ በመምጣት አንዱ ሌላው አምሳያዉን ካለምንም ርህራሄ የሚያርድበትና በጀግንነቱ የሚወደስበት ነው። ኤፒኩ ይህንን በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ህዝቦችን የማሰብ ሁኔታ በአንድ በኩል ሲያመለክት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የሰው ልጅ ተግባር ከጦርነት ባሻገር ሌላ ታሪካዊ ተልዕኮ እንዳለው የሚያመለክትና ጦርነት ለባህል ውድመትና ለሰው ልጅ ዕልቂት ምክንያት እንደሚሆን የሚያረጋግጥ ከክረስቶስ ልደት በፊት በስምንተኛው ክፍል-ዘመን የተደረሰ እስከዛሬ ድረስ ጌዜያዊነቱን ያላጣ የጭንቅላት ስራ ነው። ባጭሩ የሆሜር ኤሊያድ ፀረ-ጦርነት ኤፒክ ነው።

በዚህ እጅግ አሰቃቂ ጦርነት ውስጥ ከተካፈሉት ኦዲዩሲ ሀያ ዐመት ከተንከራተተ በኋላ ወደ ሃገሩ ይመለሳል። ሲመለስ አካባቢውንና ቤተሰቡን እንዳሉ ሆነው አላገኛቸውም። ሚስቱንና ሀብቱን ከሌላ ቦታ በመጡ ሰዎች ተነጥቋል። ደሀና ለማኝ

እንዲሆን ተገደል። የሆሜር ኤዲዬሲ የሚያሳየው በአንድ በኩል በዚያን ጊዜ የተለያዩ የግሪክ እግዚአብሄሮች እንዳሻቸው በፈለጉት ጊዜ የሰዎችን አስተሳሰብ በመጠምዘዝ ወደ ጦርነት እንደሚመሯቸው ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ኦዲዬሲ ይህንን ሁሉ አሰቃቂ ጦርነትና ከሃገር ወደ ሃገር መሰደድ ተቋቁሞ ወደ ትውልድ ቦታው እንደተመለሰ ነው። ጦርነት በሰዎች የማሰብ ኃይል ድክመት የሚቀሰቀስ እንደሆነና እግዚአብሄሮች እንደፈለጋቸው የሰውን ጭንቅላት እንደማይጠመዝዙ የተረዳበትና ቀስ በቀስም እራሱን ማግኘት የጀመረበትና ችግሮቹ የቱን ያህል ውስብስብ ቢሆኑም ብልህነትና አርቆ አስተዋይነት ከታከለበት በአሸናፊ ሊወጣና ታሪካዊ ሚናን ሊጫወት እንደሚችል የሚያረጋግጥ ኤፒክ ነው።

የሆሜር ታሪካዊ የሊትሬቸር ስራ በኋላ ለተነሱት የግሪክ ምሁሮች መመሪያ በመሆን የሰው ልጅ ሚና ከጦርነት ይልቅ ሌላ ተግባር እንዳለው የተገነዘቡበት ወቅትና አስተሳሰባቸውን በመሰብሰብ ለታላቅ ስራ እንዲነሱ በር የከፈተ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ በትንሹ አሲያ የተጀመረው የአዮውያን ስልጣኔ ታለስ ለተባለው ታላቅ የግሪክ ፈላስፋና በኋላ ደግሞ ለፒይታጎራስ የማሰብ ኃይላቸውን በማዳበር የሰውን ልጅ ታሪካዊ ሚና ለማረጋገጥ በዩኒቨርስ የተስተካከለ ውስጣዊ ህግጋትና በሰው ልጅ ጭንቅላት በስርዓት መዋቀርና መገዛት መሀከል ዲያሌክቲካዊ ግኑኝነት እንዳለ ፣ ለዚህ ደግሞ የተፈጥሮ ህግጋት በቁጥር እንደሚገለጽ ለማረጋገጥ ችለዋል። በሌላ አነጋገር የሰው ልጅ ከፍተኛ የማሰብ ኃይሉን ከተጠቀመ የመፍጠር ችሎታውን በማዳበር ራሱንና አካባቢውን በመለወጥ በሰምምነት ሊኖር እንደሚችል ነው። በአምስተኛው ክፈለ ዘመን የተነሳው ሶሎን የተባለው መሪ ይህንን መመሪያ በማድረግ በጊዜው የሰፈነውን የጭቆና አስተዳደር በአመጽ ሳይሆን በመግባባትና ሰዎችን በማሳመን በጨቋኝና በተጨቋኝ መሀከል ስምምነት ሊደረስ እንደሚችል በማሳየት በጊዜው ከፍተኛ እየተባለ የሚጠራውን የፖለቲካ ሪፎርም ያደርጋል። በቲያትርና በቀልድ ህዝቡን በማሳተፍ አስተሳሰባቸውን እንዲለውጡ በማድረግ ለግሪኩ ድሞክራሲና ስልጣኔ እንዲሁም ህዝባዊ የፖለቲካ ተሳትፎ መንገዱን ያመቻቻል። በዚህ አማካይነት ብዙ አዋቂዎችና ተመራማሪዎች ብቅ በማለት በሰው ልጅና በተፈጥሮ መሀከል ያለውን ግኑኝነት በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የሰውን ልጅ ታሪካዊ ሚናና የማሰብ ኃይል በተለያየ መልክ በመተርጎም ዕውቀትን ከጠባብ ክልልና አስተሳሰብ በማላቀቅ በሰፊው እንዲሰራጭ ያደርጋሉ። ይህ ሁኔታ በግሪክ ስልጣኔ ውስጥ ሁለት ሊገናኙ የማይችሉ አስተሳሰቦችን ይዞ ወጣ። በሶክራተስና በፕለቶ በአንድ ወገን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በቃላት ድርደራና በንግግር በተካኑት በሶፊሰቶች መሀከል የተደረገው ውይይትና ክርክር እንዲሁም ደግሞ ጥያቄዎችን እየመላለሱ ማንሳትና መልስ ለመመለስ መሞከር የሚያረጋግጠው የቱን ያህል የግሪክ ስልጣኔ ለሰው ልጅ አስተሳሰብ መዳበር በር እየከፈተ እንደመጣና የሰው ልጅም የራሱን ዕድል ወሳኝ መሆን እንደሚችል ያረጋገጠበት ወቅት ነው። ከሆሜር ጀምሮ ወደነ ታለስና ፒይታጎራስ ከዚያም ወደ ሶሎንና ፕለቶን እየዘለቀ የመጣው ፍልስፍናና የስልጣኔ ፈለግ የሰብአዊነትና የግለሰብአዊ ደርጊት ፈጠራን ያረጋገጠበት ፣ ከእንግዲህ ወዲያም የሰው ልጅ በዚህ መልክ ብቻ ራሱን በማግኘት ታሪክን እየሰራ በሰላምና በመከባበር ሊኖር እንዲችል መስመር የከፈተ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ የህብረተሰብ ግኑኝነት በተለያዩ ድሮች ሲተሳሰርና ህዝቦችም የማሰብ ኃይላቸው ሲዳብር እንዲሁም ደግሞ መሪዎች ታሪካዊና ሞራላዊ ተግባራቸውንና ግዴታቸውን ሲያሟሉ አንድ ህዝብ በዚህ በመታገዝ የውጭ ወረራን መክቶ መመለስና በድል መወጣት እንደሚችል በነሶሎን የተቀደደው የግሪክ ስልጣኔ ፈለግ ያረጋግጣል። በዚህም ምክንያት ግሪክ በጊዜው ኃያል ተብሎ በሚጠራው በፐርሺያ አገዛዝ የተሰነዘረባትን ጥቃትና ወረራ በቀላሉ ልታሸንፍ ችላለች። በሌላ ወገን ደግሞ አንድ አገዛዝ ታሪካዊ ግዴታውን ሲዘነጋ ፣ ከህብረተሰብአዊ ስምምነት ይልቅ ራሱን ከህበረተሰቡ ከፍ አድርጎ ዩኒቨርሳል መሰረተ-ሃሳቦችን ሲጥስ ህብረተሰቡንም ወደ ውርደት እንደሚጥለው ነው።

ይህ ሁኔታ የፓርመናይድስን ፈለግ ለተከተሉ ደቀ-መዝሙሮች በር በመክፈት ሰዎች በማሰብ ኃይላቸው እንዳይጠቀሙና የራሳቸው ገዢ እንዳይሆኑና ህልማቸውም በጦርነትና በስግብግብነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን መንገዱን ያዘጋጃል። ብዙ ደቀ-መዝሙሮችንንም በማሳሳት የማሰብ ኃይላቸው እንዲታፈንና አብዛኛው ህዝብ የገዢ መደቦች ተገዢ እንዲሆን በማድረግ ዕድሉ ጦርነትና መሰቃየት እንዲሆን አዲስ ፈተና ውስጥ ይከቱታል። በፓርሜናይድስ ፍልስፍና መሰረት ሀቅ(truth) የሚባል ነገር እንደሌለና አንድ ነገር ሊከፋፈል(indivisible) እንደማይችል ፣ ስለሆነም ሊለወጥና ሊንቀሳቀስ እንደማይችል ያረጋግጣል። በፓርሜናይድ ፍልስፍና መሰረት የሰው ልጅ አስተሳሰብና ዕውቀት በቀጥታ በሚታዩ ነገሮች የሚወሰን ሲሆን ፣ ከዚህ ተሻግሮ በመሄድ የተፈጥሮን ህግ በመረዳት የሳይንስና የሙዚቃ ዕውቀቶች ባለቤት አይሆንም። ይህ አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ የፒይታጎራስን ፍልስፍና ይቃወማል። እንደሚታወቀው የፒይታጎራስ መሰረታዊ

ፍልስፍና ነፍስ(soul) ከአካል(body)በላይ እንደሆነና ወደ እግዚአብሄር እየተጠጋ በመሄድ በቁጥር አማካይነት የዩኒቨርስን ህግ በመረዳት የኑሮውንም ሁኔታ መለወጥ እንደሚችል ነው። በፍልስፍናው መሰረት እግዚአብሄር ዩንቨርስን በቁጥር ውስጣዊ ህግ አማካይነት በስነስርዓት አዘጋጅቶ እንደተፈጠረ ሲያመለክት ፣ እግዚአብሄር አንድ ሲሆን ዓለም ደግሞ በተለያዩ መልኮች የምትገለጽና ብዙ ልዩ ልዩ ነገሮችን ያቀፈች ነች። ስለዚህም ማንኛውም ፍጡር እዚያው በዚያው አንድም ብዙም ነው። ለምሳሌ እንደሰው እያንዳንዳችን እንደ አንድ ሰው እንቆጠራለን። በሌላ ወገን ደግሞ ሰውነታችን ልዩ ልዩ ክፍሎች አሉት። የልዩ ልዩ ክፍላችን የተጣመሩ ስራ እንደ ሰው እንድናስብና እንድንቀሳቀስ እንዲሁም ደግሞ አዳዲስ ነገሮችን እንድንፈጥር ያስችለናል። ስለዚህም ዓለም በቅራኔ ህግጋት የምትገዛ ናት። ጨለማና ብርሃን ፣ ቀዝቃዝና ሙቀት ፣ ሰማይና ምድር ፣ በህይወት መኖርና መሞት ፣ ደስታና ሀዘን...ወዘተ. እነዚህ በአጭሩ የተፈጥሮን የቅራኔ ህግጋት ሲያመለክቱ አንደኛው ከሌላው ተነጥሎ በፍጹም ሊኖር እንደማይችል ነው። ይህ የቅራኔዎች ህግጋት መኖር ደግሞ ወደ ስምምነት የሚያመራ ነው። በዚህም ቁጥር ፣ ስምምነትና(harmony) ሙዚቃ መሰረታዊው የፓይታጎራስ ፍልስፍና ሲሆኑ ፣ ፓርሜናይድ ግን ይህንን ይቃወማል። ሶፊስቲያዊው የፓርሜናይድ መመሪያ ብዙ ተከታዮችን በመመረዝ የሚቀጥለው ትውልድ በስሜትና በራሱ ፍላጎት ብቻ የሚመራ በመሆን መስፋፋትና ጦርነት እንደ ዋና ተግባሩ አድርጎ በመውሰድ ህዝቡን ለማያስፈልግ ወረራና ዕልቂት በመዳረግ አቴንን አዳከመ። በተጨማሪም እነዚህ በፓርሜናይድ ፈለግ እንደ አሸን የፈለቁት ከህዲዎች ከጠላቶቻቸው ጋር በማበር የአቴንን ሽንፈት በማፋጠን ዝናዋን አጓደፉ። የሶፊስቶች የበላይነት ፣ በስሜትና በግብዝነት መመራት ወድቀትን ማስከተሉ የሌሎችን ሀቀኛውን መንገድ የሚፈልጉትን ሀሞት ግን ማስቆረጥ አልቻለም። ስለዚህም የጥቂት ሰዎች በስሜት መነዳት ፣ አልሰማም ማለትና አርቆ ማሰብ ያለመቻልና ይህንን በስሜት መነዳት መዋጋትና ሳይንሳዊ መሳሪያ የመፈለግ የሌሎች ታሪካዊ ተግባር ሆነ።

ይህንን የሶፊሰቶችን በስሜትና በግብዝነት ላይ የተመሰረተ ፍልስፍና ለመቋቋም ሶክራትስ ቀጥሎ ደግሞ ደቀ-መዝሙሩ ፕላቶ ከፍተኛ ትግል ጀመሩ። የሰው ልጅ አስተሳሳብ ለምን ወደዚህ አጥፊ ሁኔታ ላይ እንደሚያመራና ራሱን አጥፍቶ ህብረተሰቡንም ለውድቀት መዳረግ እንደሚችል ማውጣትና ማውረድ ጀመሩ። በሁለቱ ፈላስፎች ዕምነት መሰረት የተሳሳተ አመለካከት በጊዜው በአቴን ከተማና በተለይም በገዢው መደብና መንግስታዊ መዋቅሩ ዘንድ እንደተስፋፉና ይህንንም መቋቋም እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ የሞትና የሽረት ትግል ማድረግ ጀመሩ። ለዚህ ደግሞ ራስን በራስ መጠየቅና የአንድን ነገር አነሳስም ሆነ ምንጭ ለማግኘት ጥያቄዎችን ማንሳትና ራስን መላልሶ መጠየቅ(self intrrogation) የትግል መሳሪያና እራስን መልሶ ማግኚያ ዘዴ እንደሆነ አረጋገጡ። በመሆኑም የዕውቀት ዋናው ምንጭ ጭንቅላት እንደሆነና ሀቀኛ ሃሳብ(idea) ከጭንቅላት ውስጥ እንሚፈልቅ አረጋገጡ። ስለዚህም የሰው ልጅ በተፈጥሮ ህግ እንደሚገዛና የሶፊስቶችን አመለካከት ፣ በተለይም ህግና ዕኩልነት በገዢዎችና ኃይል ባላቸው ብቻ ተለክቶ የሚሰጥና ከዚህ ውጭ የሰው ልጅ መብት ሊረጋገጥ አይችልም የሚለውን የመጀመሪያውን የፖዘቲቭ ህግ ምንጭ የሆነውን መመሪያ ትክክል አለመሆኑን በማሳየት ለግለሰብ ነፃት የሚሆነውን መመሪያ ጣሉ። ይህንን መመሪያ በማድረግ በፐርክለስ አገዛዝ ዘመን በሶፊሰቶች አስተሳሰብ የተበከሉትን ወጣት ትውልድ ማስተማርና ጭንቅላታቸውን ማቃናት ጀመሩ። በዚህም መሰረት የሶክራትስና የፕላቶን አስቸጋሪ ግን ደግሞ ፍቱን ራስን ከቆሻሻ አስተሳሰብ የሚያላቅቅ የጥያቄና መልስ መመሪያ መፈተኛ በመሆን ወጣቱ ትውልድ ራሱን እንዲጠይቅ ፣ ለምን ይህን ሆነ ያንን የተሳሳት አስተሳሰብ እንደሚከተል ፣ ምንስ እንደሚያሰገድደው በመጠየቅ ጭንቀት ውስጥ ከተቱት። በዚህ መልክ ብቻ አንድ ህብረተሰብ ራሱን ሊለውጥና የራሱን ዕድል ሊወስን ይችላል ብለው በማመን ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት መመሪያ የሚሆን ፍልስፍና አበረከቱ።

በተለይም በሶስቱ የፕላቶን ጽሁፎች *በሪፑብሊክ* ፣ *በቲሚያውስና በክሪታስ* ውስጥ የሰፈሩት መሰረተ ሀሳቦች የሚያረጋግጡት ራስን መልሶ መላልሶ በመጠየቅ ወደ ሀቀኛው መንገድ ለመድረስ የተደረገ ፈተና ነው። በዚህም መሰረት ፣ አንድ ህብረተሰብ ከትውልድ ትውልድ በተላለፈ መጥፎ አስተሳሰብ ከተጠመደና ራሱን መጠየቅ ካልቻለና ካለወጠ ህብረተሰቡ ወደ መዝቀጥና ልቅ-አገዛዝ እንደሚወርድ ያመለክታል። በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ በስልጣን ጥም የሰከሩ የኦሊጋርኪ አገዛዛቸውን በማጠናከር ህብረተሰቡን ከአንድ አዘቅት ወደ ሌላ በመምራት ሊወጣ የማይችለው ማጥ ውስጥ በመክተት ከስልጣኔ እንዲርቅና ዘለዐለሙን በጨለማ አገዛዝ እንዲቆራኝ ያደርጉታል። በዚህም ምክንያት ሀብት ማካበትና በስልጣን መባለግ የገዢው መደብ ኖርም በመሆን ህብረተሰቡ እንዲቀበለው ያደርጋሉ። ይህ የሶክራትስና የፕላቶን ዲያሎግ የዛሬውን የኢህአዴግ የብልግና አገዛዝና ጭንቅላት መታወር ሲያረጋግጥ ፣ በዚህ አስተሳሰብ ጭንቅላታቸው እንዲታወር የተደረጉት

ካድሬዎች ወደ ጥፋት እንደሚያመሩና ህብረተሰቡን ወደ አልባሌ ቦታ በመግፋት ኑሮውን እንደሚያዘበራረቁበት ነው። ስለሆነም በሶክራቶስም ሆነ በፕላቶን ፍልስፍና መመሪያ መሰረት አንድ ህብረተሰብ ከራሱ ባሻገር ማሰብና የተፈጥሮን ህግ ተረድቶ ሁኔታዎችን መለወጥ እንዳለበት ያስተምሩናል። በፍልስፍናው መሰረት አንድ ነገር በውስብስብ መልክ ሲገኝ ፣ የአንድ ነገር ሂደትም ሆነ ዕድገት ከሌሎች ተነጥሎ በፍጹም ሊታይ እንደማይችል ያረጋግጣሉ። በሌላ አነጋገር ሰውም ሆነ በተፈጥሮ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ተደጋግፈውና በቅራኔ ህግጋት እየተመሩ ነው መኖር የሚችሉት። አንዱ ሌላውን አጥፍቶና የበላይነትን ብቻውን ተቀዳጅቶ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታም ሆነ ሃገር በፍጹም የለም። አንድ ሆነ የገዢ መደብም ሆነ ሌሎች ሀብት ያላቸው በእርግጠኝነት መኖር የሚችሉት የሌሎችንም ፍላጎትና የመኖር መብት ሲያውቁና በዩኒቨርሳል ህግ መሰረት ሲመሩ ብቻ ነው። አንደኛው የህብረተሰብ ክፍል ተንደላቆ እየኖረ ሌላው ደግሞ በድህነት እየማቀቀ አንድ ህብረተሰብ ጤናማ ሊሆን በፍጹም አይችልም። በአንድ ህብረተሰብ ወስጥ የተወሰኑ በጠቅላላው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ኖርሞች መኖር አለባቸው። መደጋገፍና ለሌላው ማሰብ ህብረተሰብአዊ ኖርሞች ናቸው። እኩልነት የሚለውም መሰረተ ሃሳብ ከዚህ የመነጨ ሲሆን ፣ኖርማቲቭ ባህርይ ነው ያለው። በሌላ አነጋገር ፣ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በመቀስ እንደተከረከሙ ዛፎች እኩል ይሆናሉ ማለት ሳይሆን ህብረተሰብአዊ ሚዛን እንዳይናጋ መጠበቅ ያለባቸው የህብረተሰብ ህጎች መኖራቸውን ነው የሚያመለክተው። የዲሞክረሲው መሰረተ-ሃሳብም ይህ ነው።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ይህ ወርቅና ብሩህ መመሪያ እያለ ታዲያ የሰው ልጅ ለምን እየመለሰ እየመላለሰ ወደ አዘቅት ውስጥ ይወድቃል? ለምንስ የራሱን ዕድል በራሱ መወሰን ይሳነዋል? ለምንስ በጥቂት አሳሳቾች በመመራት ወደ ጥፋት ያመራል ? እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ጭንቅላት የተረጋጋ አይደለም። ተለዋዋጭ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ አስቸጋሪውንና ግን ደግሞ ወደ ሀቅ የሚመራውን መንገድ ከመፈለግና እሱን ከመከተል ይልቅ ቶሎ ብሎ ሀብት ሊያገኝ የሚችልበትን ወይም ደግሞ ደስታን የሚጎናጸፍበትን መንገድ ይከተላል። ይህንን የተገነዘቡ ጥቂት ለስልጣን የቋመጡ የውሸት ቅስቀሳና ስሜታዊ ንግግር በማድረግ አንድ ህብረተሰብ ቀናውን መንገድ እንዳይከተልና ጭንቅላቱ እንዲታወር ያደርጋሉ። ተረጋግቶ እንዳይኖር በማድረግ ዓላማው በስግብግብ ዐለም ውስጥ እንዲሽከርከር በማድረግ አንዱ ሌላውን እየፈራና እየተጠራጠረ እንዲኖር ያደርጋሉ። በዚህ ላይ ደግሞ ሀይማኖትና ባህላዊ የአኗኗር ዘዴዎች ሲታከሉበት አንድ ህብረተሰብ ራሱን ማግኘት ይሳነዋል። ጭንቅላቱ በመጋረድ በቀላሉ የሚያያቸውንና ሊፈታቸው የሚችላቸውን ችግሮች እንዳይፈታ ይታገዳል። በዚህ መልክ የአንድ ህብረተሰብ ጭንቀትና በችግር ዐለም ውስጥ መኖር ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ህብረተሰቡ እየተደናበረ እንዲኖር ይረገማል። በዚህም ምክንያት በአውሮፓ ውስጥ በተለይም በግሪክ የተጣለው የመጀመሪያው የሳይንስ ፈለግ ተግባራዊ ለመሆን የቻለው ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዐመት በኋላ ነው። ለዚህም ነው የአውሮፓ ህዝብ ለብዙ መቶ ዐመታት በጨለማ ዘመን መኖር የተገደደው። ይህንን የጥቂት ሰዎችን ድብቅ ዓላማና አንድ ህብረተሰብ ለምን ዘለዐለሙን በጨለማ ዐለም ውስጥ ተረግሞ ይኖራል ብለው ሊጠይቁና ሊረዱ የሚችሉት ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ናቸው። በዚህም ምክንያት ውሸትና ውሸተኞች የበላይነትን እየተቀዳጁ ይኖራሉ። የሰው ልጅም በየጊዜው በሚፈራረቁ ሁኔታዎች እንዲኖር ይገደዳል።

እንደዚህ ዐይነቱ ውሸት መንገስና ሰዎችም በጨለማ ዐለም ውስጥ መኖር በአውሮፓ ምድር ውስጥ በተለይም በጣሊያን ተስፋፍቶ ነበር። በአስራሶስተኛው ክፍለዘመን የጣሊያን ህዝብ በጨለማ ዐለም ውስጥ የሚኖር ነበር። ህበረተሰቡ የሚገናኝበትና የሚግባባበት አንድ ቋንቋ አልነበረውም። ሁሉም የተሰባበረና የራሱን ዲያሌክት ስለሚናገር የህዝቡን ጭንቅላት አድሶ ሳይንስን ለማዳበርና አዲስ ህብረተሰበ ለመገንባት አስቸጋሪ ነበር። የተለያዩት ዲያሌክት ቃላቶች በጣም ረጃጅሞች ስለነበሩ የቋንቋን ሳይንስ አሰካክና ሰዋሰው ተክትለው የተዘጋጁ አልነበሩም። በዚህም ምክንያት የሰውን ጭንቅላት የመረበሽና የመበታትን እንዲሁም ደግሞ የራሱን ሚና እንዳይረዳ ያላቸው ኃይል ከፍተኛ ነበር። የኢጣሊያን ህብረተሰብ በጨለማ ዐለም ውስጥ መኖሩን የተረዳው ዳንቴ የተባለው ፈላስፋ የቋንቋ ህግ መመሪያ ያወጣል። የማያስፈልጉና አንድን ቃል የሚያንዛዙ ፊደሎችን በማውጣት ሳይንሳዊ ፈለግ እንዲይዙ ያደርጋል። ፍቅር ፣ ምኞት ወይም ፍላጎት ፣ ዕድል ፣ መስጠትና ደስተኝነት የሚሉት ፅንሰ-ሃሳቦች ህብረተሰብአዊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረግ ህዝቡ በህግ እንዲገዛና የሞራል ብቃት እንዲኖረው እንዲሁም ደግሞ አንዱ ለሌላው ማሰብ እንዳለበት ያስተምራል። በዚህ መሰረት ብቻ አንድ ህብረተሰብ ችግሮችን ሊወጣና ርስ በርሱ በመግባባት ወደፊት መጓዝ እንደሚችል ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ለመጪው ትውልድ መመሪያ የሚሆን ህብረተሰቡን ከጨለማ የሚያወጣ የእግዚአብሄሮች ኮሜዲ የሚለውን ታላቅ መጽሀፍ ይጽፋል። ይህ መጽሀፍ ለሬናሳንስ በር በመክፈት ተዓምር እንዲሰራ ያደርጋል።

በኮሜዲው ውስጥ ዳንቴ የሚያመለክተው የመንፈስን ከጨለማ ወደ ብርሀን ጉዞ ነው። በመጀመሪያው ጉዞው ፣ ዳንቴ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በገሀነመ-እሳት ውስጥ እንዳለ ይገነዘባል። በዚህም መሰረት ትልቅና አንድ ወጥ መንገድ የሌለው በአውሬዎች በተከበበ ጫካ ውስጥ እንደተጣለ ይገነዘባል። አውሬዎች ሊበሉትና ሊቃረቱት ሲያሯርጡት በጭንቀት ዐለም ውስጥ እንዳለ ይረዳል። በዚህ ጭንቀት ዓለም ውስጥ እንዳለ ቨርጂል የምትባል በቢያትሪክስ ተልካ እንደመጣችና ከዚህ ጨለማና አስፈሪ ዐለም ውስጥ እንደምታወጣውና ወደ ጸጋውና ገነቱ ዓለም ውስጥ እንደምትመራው እንደተላከች ታበስርለታለች። ለምን እኔን ብቻ ብሎ ይጥይቀታል። እሷም ይህንን አሁን ልነግረህ አልችልም ትለዋለች። በመጀመሪያው ጨለማውንና ጠመዝማዛውን መንገድ መጨረስ እንዳለበት ታስረዳዋለች። ዳንቴ ግን ከዚህ ጭንቀት ለመውጣት ቶሎ ቸኮለ። ይሁንና ፍቅር እንደምትከተለው ስለተረዳ በመጀመሪያ ፈተናውን ማለፍ እንዳለበት ተረዳ። ይህ ገሀነመ እሳት ግን በእርግጥ የሚኖር አይደለም። ሜታፎራዊ አነጋገር ሲሆን የእንግሊዙን ፈላስፋ የሆበስን ግለሰብአዊ ጥቅምን ማሳደድ የሚያመለከት ፣ *የስግብግብነት ፣ የራስን ፍላጎት ብቻ* የሚያሟላ ዓለም ነው። ስለዚህም ገሀነመ-እሳት ፍርሀትን ፣ ስግብግብነትን ፣ በጊዜያዊ ጥቅም መደለልንና ክብርን መሸጥ እንዲሁም *ቂም-በቀልነትን* የሚገልጽ የአእምሮ በሽታ ነው። ሰዎች አርቀው ማሰብ ሲሳናቸው ክፉ የተባለውን ነገር ሁሉ ከማድረግ መቆጠብ እንደማይችሉ የሚያመለክት ትልቅ የጭንቅላት በሽታ ሲሆን ፣ ጥቂት ሰዎች በተወሰነ አስተሳሰብ ውስጥ በመዋዠቅ ወደ ጥፋት እንደሚያመሩና ለሌላውም እንደሚተርፉ ዳንቴ ያስተምረናል።

በመቀጠልም ፣ ዳንቴ በጉዞ ላይ እንዳለ ከሀጢአተኞች ጋር ይገናኛል። ዘለዓለማቸውን ሙቀትና ቀዝቃዛ ውሃ እየተፈራረቀባቸው በሰሩት ሀጢአት እየተወነጀሉ እንደሚኖሩ ይገነዘባል። እነዚህ ሀጢአተኞች የማሰብ ኃይላቸውን መጠቀም ያልቻሉና በእግዚአብሄር የሚያሾፉ ናቸው። የተፈጥሮን ህግ በመጣስ በምድር ላይ በነበሩበት ዘመን ብዙ ሀጢት የሰሩ ናቸው። እነዚህን ሁሉ ይመለከታል። ይህ በእንደዚህ እያለ አንዱ ሀጢአተኛ በሀጢአቱ ከመጸጸቱ ይልቅ መጥቶ ይጮህባቸዋል። እግዚአብሄርንም ይሳደባል። ዳንቴ እዚህ ላይ የሚያመለክተው የብዙ ሰዎችን በወንጀላቸውና በሀጢአታቸው ለመጸጸት አለመቻልና ወደ ቀናው መንገድ ተመልሰው ጥሩ ነገር ለመስራት ጥረት ያለማድረግ ነው። በአርቆ አስተሳሰባቸው መጠቀም የማይችሉ ከአንድ ስህተት ወደ ሌላ በመሸጋገር ራሳቸውን አሰቃይተው ሌላውንም ለጥፋት የሚዳርጉ መሆናቸውን የሚያመለክት ትምህርት ነው። በዚህ መልክና ውስብስብ የጨለማውና አስፈሪው ጉዞው ዳንቴ ብዙ ሀጢአተኞችን ፣ ነፍስ አጥፊዎችን ፣ ከሀዲዎችን ፣ ሃገር ሻጪዎችን ፣ ቀጣፊዎችንና የተፈጥሮ ህግጋትን የሚጥሱትን የዝሙት ስራ ፈጻሚዎችን በሙሉ ይመለከታል። ያዝናል ፣ ይጸጸታል። ስለዚህም ራስን ከዚህ ሀጢአት ለመላቀቅና ቀናውን መንገድ ለመያዝ የግዴታ ራስን ማጽዳት እንደሚያስፈልግ ይገነዘባል። በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ግን ደግሞ በሚቻል ራስን የማጽዳት ዘመቻ የሰው ልጅ በስምምነት በመኖር በምድር ላይ ገነትን መመስረት እንደሚችል ያመለክታል። ይህ ኮሜዲያ ለሚቀጥለው ትውልድ መመሪያ በመሆን በኢጣሊያን ምድር እንደነ ሊዎናርዶ ዳቪንቺና ሚካኤል ኤንጀሎ እንዲሁም ለፔትራርካስና ሌሎች የሳይንስና የፈላሰፋ ሰዎች ትምህርት በመሆን ሬናሳንስ ለተባለው ታልቅ እንቅስቃሴ በር ይከፍታል። ከዚያ በኋላ ነው በኢጣሊያን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ትልቅ የጭንቅላት እንቅስቃሴ የተጀመረውና ቀስ በቀስ ግን ደግሞ በእርግጠኝነት ውጤት እያሰገኘ የሄደው። በዚህ ከፍተኛ የጭንቅላት ስራም ነው ብዙ የአውሮፓ ሃገሮች ከድህነት ፣ ከረሀብ ፣ ከተስቦና ከወባ በሽታ በመላቀቅ ዕወነተኛ ነፃነትን መቀዳጀት የቻሉት። እንደነ ኩዛኑስ ፣ ኬፕለርና ላይብኒዝ የመሳሰሉት ፈላስፎችና የሳይንስ ሰዎች ሊፈልቁና የአውሮፓን ዕድገት አቅጣጫ ሊያሲዙ የቻሉት በዚህ በግሪክ ፈላስፎችና በዳንቴ በተቀደዱት መመሪያዎች ብቻ በመመራት ነው።

በአውሮፓ ምድር እንደዚህ ዐይነት ከፍተኛ ጭንቅላትን የሚያድስና ታሪክን የሚያሰራ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ተካሄዶና ፍልስፍናው እጅግ በአማሩ ከተማዎችና የቤተክርስቲያን አሰራሮች ተግባራዊ ሆኖ አሁንም የአውሮፓ ህዝብ እየተመላለሰ ለጦርነትና ለበሽታ የተጋለጠበት ዘመን ነበር። በሀይማኖት ልዩነት ተሳቦ በፕሮቴስታንቶችና በካቶሊኮች መሀከል የተካሄደው ሰላሳ ዐመት የፈጀ መጨፋጨፍ ለብዙ ሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገበሬ በዚህ አረመኔያዊ ርስ በርስ መጨፋጨፍ በመሞቱ በብዙ ቦታዎች የምርት እንቅስቃሴዎች ተዳክመዋል። ከተማዎች ፈራርሰዋል ፤ የንግድ እንቀስቃሴዎች ተዳክመዋል። በሴቶች ላይ የተካሄደው የማቃጠል ዘመቻ ለብዙ ሴቶች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። እነዚህ ሁሉ የሰውን ህይወት ጨራሽ ጦርነቶችና ሃገር አፍራሽ ተግባሮች የተካሄዱት በተራው ህዝብ አማካይነት አይደለም። በገዢዎችና በሀይምኖት መሪዎች በተቀሰቀሰ ጦርነት ምክንያት ነው። ገዢዎችና

የሀይማኖት መሪዎች አርቆ አስተዋይነታቸውን ከማስቀደማቸው ይልቅ በስሜት እየተገፋፉ ባካሄዱት ግብግብ ነው። ይህንን ሁኔታና በተለይም ደግሞ በመጨፋጨፍ ምንም ዐይነት ህብረተሰብአዊ ለውጥ ሊመጣና ተደላድሎ መግዛት የማይቻል መሆኑን የተረዱት በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ ዘመን ብቅ ያሉት ፈላስፎች ፣ የግጥምና የቲአትር ሰዎች ማስተማር የጀመሩት አሁንም ቢሆን የግዴታ የሰው ልጅ በከፍተኛ ደረጃ ጭንቅላቱን በማደስ ራሱን ማግኘት እንዳለበት ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱ ህይወት ባለቤት ሲሆንና በዚህች ምድር ታሪካዊና የሞራል ኃላፊነት ያለው መሆኑን ሲረዳ ብቻ ትርጉም የሌለው የርስ በርስ ጦርነት እንደሚቆም ወይም እንሚወገድ በተለይም ሺለር የተባለው የጀርመን የቲያትር ፣ የግጥምና የታሪክ ደራሲና ተመራማሪ በመቶ በሚቆጠሩ ጽሁፎቹ ያመለክታል። አንድ የጀርመን ጸሀፊ ይህንን አስመልክታ ባስቀመጠችው መሰረት የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ዘዴውን ካልለወጠ(Method of thought) መልሶ መላልሶ የሰራውን ስራ እንሚያወድምና እንደገና ሀ ብሎ እንደሚጀምር ታስገነዝባለች። „ Schiller sees the way toward ennoblement of the individual, upon which all improvement in political affairs depends, in the education of emotions up to those airy heights where those emotions correspond with reason. Only if the individaul person perfects himself, will the character of the nation be improved, and only then does political progress occur.” በሌላ አነጋገር አንድን ህዝብ ነፃ የሚያወጣውና ታሪክ እንዲሰራ የሚያስችለው አንድ መሪ ነኝ የሚል ትልቅ ዲስኩር ስለሰበከ አይደለም። አንድ ህዝብ የስልጣኔ ባለቤት መሆን የሚችለው እያንዳንዱ ግለሰብ አርቆ የማሰብ ኃይሉን በመጠቀም ራሱ የራሱ ዕድል ወሳኝ መሆኑን ሲረዳ ብቻ ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ የአንድ ህብረተሰብ አካል መሆኑን ሲረዳና አንዱ ከሌላው ተነጥሎ ብቻውን መኖር እንደማይችል የተገነዘበ ብቻ እንደሆነና ልዩነትን በውይይት ብቻ በመፍታት ልዩነትና አንድነት ተጣምረው ሊሄዱ የሚችሉ ፣ አንደኛው ከሌላው ተነጥሎ ሊጓዝ መሄድ የማይችል መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው። በዚህ ዐይነቱ ሰላምንና ብልጽግናን አጎናጻፊ እንቅስቃሴ ውስጥ የምሁሮች ሚና ከፍተኛ ቦታ ይኖረዋል። ደራሲዎችና የቲአትር እንዲሁም የስዕልና የአርክቴክቸር ሰዎች በታሪክ ወስጥ የግለሰቦችን አስተሳሰብ በማነጽ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታሉ። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው አሁንም እነዚህ ምሁራን በትክክለኛ ፍልስፍና ሲመሩ ብቻ ነው። የተዘበራረቀ ዕውቀት በሰፈነበት ዐለም ውስጥ ከቶውንም ጭንቅላት ዕውነተኛ ተሀድሶ ሊያገኝ በፍጹም አይችልም። ይህንን በሚመለከት አዋቂዎች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን ታሪካዊ ሚና ፍሪድርሽ ሺለር በብዙ ጽሁፎቹ ውስጥ ያመለክታል። በተለይም ፣ “ምን ማለት ነው?ለምንስ ፍጻሜ አንድ ሰው የዓለምን ታሪክ ማጥናት አለበት”(What is, and to What End do we study universal history ?) በሚለው ለተማሪዎች ባቀረበው ትምህርታዊ ጽሁፍ ፣ የሰው ልጅ ታሪክ በጣም ሰፊና ፍሬያማም እንደሆነ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ አርቆ ማሰብ በመቻሉም ሆነ ይህንን ባለመጠቀሙ እየተፈራረቀ ለታሪክ ስራም ሆነ ጥፋት ራሱ ተጠያቂ እንደሆነና የሞራል ብቃትነቱም ሆነ ድክመቱ በዚህ የታሪክ ስራ ውስጥ እንደሚሽከረከርና ማንኛውም ትውልድ ይህንን ማጥናት እንዳለበት ምክር ይለግሳል። የፍሪድርሽ ሺለር የዩነቨርሳል ታሪክ አተናተን እንደማንኛውም የታሪክ ጽሁፍ አቀራረብ ሳይሆን የሰውን ልጅ ደካማና ጠንካራ ፣ አስተዋይነትና በሌላ በኩል ደግሞ በስህተት ዓለም ውስጥ ዘፍቆ ራሱን እንደሚያሰቃይ ነው የሚያመለክተው። ስለዚህም ይላል ፍሪድር ሺለር ፣ የሰው ልጅ በታሪኩ ውጥ እየተነሳና እየወደቀ ታሪክን መስራት እንደቻለ ፣ ዕደ-ጥበብን እንዳደበረ ፣ ከተማዎችን እንደመሰረተ ፣ ንግድን ማስፋፋት እንደጀመረና በዚህ አማካይነት እየተሳሰረ እንደመጣና ባህልን ማዳበር እንደጀመረ እጅግ በሚጥም መልክ ያቀርባል። ስለሆነም የሰው ልጅ ከፈለገና ካሰበበት ከፍተኛውን የሞራል ብቃት በማግኘት ታሪክን እየሰራ በስምምነት ሊኖር እንደሚችል ያመለክታል። በፍሪድሪሽ ሺለር ዕምነትም ድራማና ሌሎች ልዩ ልዩ ጥበቦች የሰውን ልጅ ጭንቅላት በመኮትኮት ከፍተኛ ሚናን እንደሚጫወቱ ያብራራል።

## <u>የአእምሮና የመንፈስ ዕድገት ሁኔታ ድርጌታችንን ይወስናሉ</u>

### ከአጠቃላዩ ወደ ተጨባጭ ትንተና

የማንኛውም ሰው ድርጊት በአዕምሮው ሆነ በመንፈሱ ትዕዛዝ እንደሚወሰን ፈላስፎችም ሆነ የህሊና ሳይንስ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ። የየግለሰቦችም መጥፎና ጥሩ ድርጊት ከልጅነት ጀምሮ በአስተዳደጋቸውም ሆነ በአካባቢያቸው በሚያዩትና ሳያወቁ በሚቀስሙት እንዲሁም ደግሞ ከትምህርት ቤት በሚያገኙት የትምህርት ዐይነት ይወሰናል። ፕላቶ እንደሚለው ከሆነ ማንኛውም ሰው ከተደበቀ ሃሳብ ጋር እንደሚፈጠር ሲያስረዳ ፣

በዐይን የሚታዩ ተጨባጭ ነገሮችም ሆነ ሁኔታዎች ሃሳብን በመገንባትና በድርጊት ላይ ሚና እንዳላቸው ይናገራል። አሪስቶትለስ ግን የአንድ ሰው አስተሳሰብ በሚታዩ ነገሮች ብቻ እንደሚቀረጽና ድርጊቱን እንደሚወስን ያመለክታል።

በሶክራተስም ሆነ በፕላቶን ፍልስፍና መሰረት መንፈስ(Soul) በሰው ልጅ ህይወት ወስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። ፕላቶን ህግ( the Law) በሚለው መጽሀፉ ውስጥ መንፈስ እራሱን በራሱ የሚያንቀሳቅስ ኃይል( self-initiating motion) ነው ብሎ ያስቀምጣል። ስለዚህም በአካል ላይ የበላይነት እንዳለውና የአዋቂነት ምንጭ(intelligence) እንደሆነ ይገልጻል። ይሁንና ይላል ፕላቶን ፣ ከውጭ ወደ ጭንቅላት ውስጥ የሚገቡ መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገሮች በመንፈስ ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖራቸው ሲገልጽ ፣ በተለይ መጥፎ አስተዳደግና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣ ባህል መንፈስን የመረበሽ ባህርይ እንዳለው ወይም ጭንቅላትን እንደሚጋርድ ይናገራል። „No one is willingly bad; the bad man becomes bad because of some faulty habit of body and a stupid upbringing, and these are unwelcome evils that come to any man without his choice.“ በፕላቶን የህሊና ሳይንስ መሰረት መንፈስ በሶስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ፣ እነሱም አርቆ የማሰብ ወይም ነገሮችን የማመዛዘን ክፍል ፣(the rational part) የመንፈስ ጥንካሬ ያለው ክፍልና(the spirited part) ስግብግብ ወይም በቀላሉ ሊታለል የሚችል (the appetitive part) ክፍል ናቸው። እነዚህ የተለያዩ ክፍሎች ግን እዚያው በዚያ እንዳሉና እንደተጨባጭ ነገር ተከፋፍለው እንደማይገኙ ማጤን ያስፈልጋል። ከነዚህ ሶስት ክፍሎች ውስጥ የመንፈስ ጥንካሬ ክፍል ከፍተኛውን ቦታ ሲይዝ ሊሞት የሚችል እንዳይደለ ፕላቶን ይገልጻል። ስለዚህም አርቆ የማሰብ ኃይል ክፍል ወደ መንፈሳዊው ጥንካሬ ክፍል የሚጠጋ ሲሆን በሰዎች ድርጊት የሚገለጽ ነው። በሌላ አነጋገር እንደ ሰዎች የመንፈስ ጥንካሬ ደረጃነት አርቆ የማሰብም ሆነ ያለማሰብ ኃላቸው ይወሰናል ማለት ነው። የመንፈስ ጥንካሬ በራሱ ደግሞ በየጊዜው ራስን ከመጠየቅና ጭንቅላትን ከማደስ ጋር ተያይዞ የሚሄድ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዘው ተንኮል ወይም ተንኮል አለመስራት ፣ ርህራሄነት ወይም አረመኔነት እዚያው በዚያው የሚገኙ ናቸው። እነዚህ የተለያዩ ድርጊቶችም ሊገለጹ የሚችሉት እንደ የግለሰቡ የመንፈስ ጥንካሬና መላላት ሁኔታ ነው። ይህ የፕላቶን መንፈስን በሶስት መከፋፈል በሰው ልጅ ጭንቅላት ውስጥ የማያቋርጥ ትግል እንዳለ የሚያሳይ ነው። የሰው ልጅ አስተሳሰብ ተለዋዋጭና እንደየ ሰው አስተዳደግ ፣ ያለበት አካባቢና የዕውቀት ዐይነት እንደየሁኔታወ ሊፈራረቅ እንደሚችል ነው የሚያመለክተን። የሺክሰፐርም ስራ ይህንን የሰዎችን አስተሳሰብ በጉዞ ላይ እንዳና ተለዋዋጭ እንደሆነ ነው የሚያረጋግጥልን።

ይህንን የፕላቶንን የህሊና ሳይንስ ወይም የመንፈስ አገላለጽ ከሌሎቹ ስራዎች ነጥሎ በፍጹም ማየት አይቻልም። ሰለ ሰው ልጅ ስነ-ምግባርና ግብረ-ገብነት የተደረሱት ስራዎች ከመንፈሳዊ ጥንካሬ ጋር በጥብቅ የተያያዙ ፣ ሲሆን በሰው ልጅ ድርጊት ላይም ከፍተኛ ተጽዕኖ አላቸው። በተለይም ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ ዕወቀት በሰዎች አርቆ የማሰብ ኃይልና ደርጊታቸው እንዲሁም ደግሞ አንድን ህብረተሰብ በመገንባትም ሆነ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ በመምራት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህም በሶክራተስም ሆነ በፕላቶን አመለካከት በቀጥታ የምናያቸው ነገሮች (sense perception) የዕውቀት ምንጭ ሊሆኑ አይችሉም። በሌላ አነጋገር አይቶ ፍርድ መስጠትና በዕውነተኛ ዕውቀት መሀከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። ሰለዚህም እያንዳንዱ ግለሰብ የአንድን ነገር ምንነት ወይም ሁኔታ በሌላ መልክ ሊተረጉመው ወይም ሊረዳው ስለሚችል ይህ በቀጥታ የምናየው ሁኔታና ያንን እንዳለ ለመግለጽ የምናደርገው ሙከራ የዕውቀት ምንጭ ሊሆኑ አይችሉም። የዕውቀት ዋናው ምንጭ አንድ ሁኔታ ለምን እንደዚህ እንደሚሆን ፣ ለምን በሌላ መልክ ለመገለጽ እንደማይችል ተደጋግሞ ጥያቄ ሲነሳና አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ሲሞከር ብቻ ነው። ሰለዚህም ዕውነተኛ ወይም ትክክለኛ ዕውቀት ዕውነትን ያዘለ ወይም የሚያሳስት አይደለም። በመሆኑም ዓለም አቀፋዊና ሳይንሳዊ ባህርይ ያለው ነው። ይህንን ለመረዳት ቀላል ምሳሌ እንውሰድ። ለምሳሌ በዓለም ላይ ያለውን የኃይል አሰላለፍና በተወሰኑ ሃገሮች ለረጅም ጊዜ የሰፈነ ድህነት እንደ ተፈጥሮአዊ አድርገው የሚቆጥሩና ይህም ሁኔታ በጥቂት ሃገሮች ችሮታ ብቻ ጋብ ሊል እንደሚችል የተገነዘቡና ይህንንም እንደ ዕውቀት አድርገው የሚያስተምሩ ኢኮኖሚስቶች በየቦታው አሉ። በዚህም ምክንያት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ለማሳሳትና አደንቁሮ ለመግዛት በየጊዜው አዳዲስ ሞዴሎች ይወጣሉ። ድህነትን የሚያራዝሙ ፤ ያለውን ያህል ሚዛን የሚያጠነክሩ። ስለዚህም የእያንዳንዱ ህብረተሰብ ጥረት የእንደዚህ ዐይነት አሳሳች ሞዴሎችን የርዕዮተ-ዓለም ምንጭ በመገንዘብ ካለበት ችግር ለመውጣት የሁኔታውን አመጣጥ ታሪክ ሲያጠና ፣ በቀጥታ ከሚያየው ሁኔታ ባሻገር ጠለቅ ብሎ ሲመራመርና ለችግሩ ትክክለኛ መፍትሄ ለመስጠት ትግል ሲያደርግ ብቻ ነው። ስለዚህም ዕውቀትንና የዕውቀትን ምንጭ በሚመለከት ከጥንታዊቱ ግሪክ ጀምሮ እስከ አሁን

ድረስ ከፍተኛና ያልተቋረጠ ትግል ተካሂዷል። እየተካሄደም ነው። ለዚህም ነው በዓለም ላይ ጦርነትና ድህነት በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሀብትና ቅንጦ የአኗኗር ስልቶች እዚያው በዚያው ተፋጠው የሚታዩት። ለዚህም ነው እንደኛ ያለው ምስኪን የዝንተ-ዓለሙን በድህነትና በጦርነት ዓለም ውስጥ ዘፍቆ ችግሮችን መፍታት ተስኖት እየለመነ እንዲኖር የተገደደው።

የፕላቶንን ፍልስፍናና የዕውቀት ምንጭ ኒኮላውስ ኩዛኑስ የተባለው ሳይንቲስትና ቄስ እንዲሁም የካልኩለስን ሂሳብ አንደኛውን ክፍል ፈጣሪ ፍልስፍናውን በማዳበር ማንኛውም ግለሰብ አንድ ነገር የመረዳት ፣(the power of understanding) አርቆ የማሰብ ኃይል እንዳለው ፣(the pwer of reasoning)ነገሮችን መገመት እንደሚችል ወይንም በጭንቅላቱ ውስጥ እንደሚታዩት ፣(the power of imagining) አንድን ነገር እንደሚቀስምና ግምት እንደሚሰጥ(the power of percieving) ያረጋግጣል። ስለሆነም ይላል ኩዛኑስ ፣ የሰው ልጅ አእምሮ አንዱን ነገር ከሌላው የመለየት ፣ የማወዳደር ፣ የማደባለቅ ወይም የማዋሀድ ፣ የመነጣጠል ፣ የማወቅ ፣ አርቆ የማየት ፣ የመከፋፈልና ስም የመስጠት ኃይል አለው ብሎ ያስረዳል። ይህ ማለት የአእምሮአችን አገነባብ አንድ ወጥ ነው ማለት አይደለም። በአንድ ጊዜ ብዙ ነገሮች የሚታዩትና ለመለያየት የሚችል ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ማሰብ ሲቻልና በትክክለና ዕውቀት ሲገነባ ብቻ ነው።

የኩዛኑስ አተናተንን ትክክል መሆኑን በመቀበል ወደ ህሊና ሳይንስ ስንመጣ ደግሞ ከፍሮይድ ለየት ያለ አመለካከት ያለው ፍሪድሪሽ ኸርበርት የሚባለው የህሊና ሳይንስ ተመራማሪ ለአንድ ሰው አእምሮና መንፈስ መገንባት አስተዳደጉ ፣ የትምህርት ዐይነትና አሰጣጥ ዘዴዎች እንዲሁም የህብረተሰቡ የባህል ሁኔታ እንደሚወሰኑ ይናገራል። በአዕምሮና በመንፈስ መሀከል የጠበቀ ግኑኝነት መኖሩን በማረጋገጥ ፣ አንድ አስተማሪ ተማሪው በትክክል እንዲያስብ ፣ በነገሮች መሀከል መተሳሰር እንዳለ እንዲረዳ ፣ ይህንንም ውጭ ከሚያያቸው ነገሮች ጋር በማገናኘት የማሰብ ኃይሉን ማዳበር እንዳለበት ያመለክታል። ስለዚህም ይላል ፣ የማሰብ ኃይል ዕድገት ሁኔታ ከፍተኛ ቦታን ሲይዝ ፣ በየጊዜው በቀጥታ ከሚያያቸው ነገሮች ጋር መነጋገርና ዕድገታቸውን መከታተልና ሁኔታዎችን መቀየር እንዳለበት ይገልጻል። በመሆኑም ምን ዐይነት አስተሳሰብ ወደ ጭንቅላት ውስጥ እንደሚገባና የአንድን ልጅ የማሰብ ኃይል ጥሩም ሆነ መጥፎ በማድረግ ድርጊቱን እንደሚወስን ያስረዳል። ሪማን የተባለው የጋውስ ተማሪና የሂሳብ ሊቅ ይህንን ሃሳብ በማጠንከር የፍሪድሪሽ ኸርበርት ምርምር የቱን ያህል ለሂሳብ ፈጠራው እንደረዳው ይናገራል። ሪማን ጠለቅ እያለ ባሰበ ቁጥር አዳዲስ ሃሳቦች እንደፈለቁለትና የድሮዎችን ከአዲሶቹ ጋር በማጣመር የማሰብ ኃይሉን እንዳዳበረና አዲስ የሂሳብ ምርምር(set theory) መፍጠር እንደቻለ ይናገራል።

ፍሮይድና የፍሮይድን አስተሳሰብ የሚከተሉ ሰዎች አንድ ሰው ባደገበት ቤተሰብ ውስጥ በሚያገኘው ፍቅርም ሆነ ለማግኘት ባልቻለው ቤተሰብአዊ ፍቅርና እንክብካቤ አስተሳሰቡም ሆነ ድርጊቱ ሊወሰን እንደሚችል ይናገራሉ። የየግለሰቦችም መጥፎ ድርጊት ከዚህ በበቂው በልጅነት ጊዜ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ካለመቻልና ቤተሰብአዊ ፍቅርን ከማጣት ጋር እንሚያያዝ ይናገራል። ኤሪሽ ፍሮም  የተባለው ማርክሲስታዊ የህሊና ሳይንስ ተመራማሪ "ህብረሰብአዊ የህሊና ሳይንስና የህብረተሰብ ቲዎሪ" በሚለው መጽሀፉ ውስጥ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየ የአኗኗር ስልት ፣ የአመራረት ዘዴና የምርት ግኑኝነት ሁኔታ በሰዎች አስተሳሰብና ድርጊት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚኖረው በደንብ ያሰቀምጣል። ለምሳሌ አንድ የፊዩዳል ህብረተሰብ ውስጥ የተወለደና እዚያው ያደገ ዘመናዊ ትምህርት ቢቀስምም የማሰብ ኃይሉና ድርጊቱ በዚያው በፊዩዳል ስርዓት ይወሰናሉ ማለት ነው። ዛሬ በዓለም ላይ ያለውን ህብረሰብአዊ ችግር ለመፍታት የሚደረገውን ትግል ስንመለከት አብዛኞች የሶስተኛው ዓለም ሃገሮች ችግራቸውን ለመፍታት የሚያስችላቸው ሳይንሳዊ መሳሪያ እንደሌላቸው መገንዘብ እንችላለን። አርቆ ማሰብን ከመጠቀም ይልቅ ጉልበትን ያሰቀድማሉ። ህብረተሰብአዊ ሚዛን ለማምጣት ጥረት ከማድረግ ይልቅ የማይሆን ፖሊሲ በመከተል ህብረተሰብአዊ ትርምስ እንዲፈጠር ሳያስቡት መንገዱን ያመቻቻሉ። የማያስፈልግ እልክ ውስጥ በመግባት ለዕድገትና ለስልጣኔ እንቅፋት ይሆናሉ። በዚህም የህብረተሰብአቸው ዕድል በህዝቡና በኤሊቱ መሆኑ ቀርቶ በውጭ ኃይሎች እንዲወሰን ያደርጋሉ። ይህም ማለት ይህ በፍሮይድ የህሊና ሳይንስ ላይ የተመሰረተው የኤሪሽ ፍሮም ትንተና የአንድ ህብረተሰብ የባህል ዕድገት ሁኔታና የማቴሪያል ሁኔታዎች ለአንድ ልጅ የማሰብ ኃይል ዕድገት ወሳኝ ሚናን እንደሚጫወቱ ነው የሚያረጋግጠው ። ይህም ማለት ስለ አንድ ግለሰብ አስተሳሰብና ድርጊት ፍርድ ከመስጠታችን በፊት የግለሰቡን ሁለመንታዊ ሁኔታ መመርመር ያሰፈልጋል። ማንኛውም

ሰው አረመኔ ሆኖ ወይም ዲሞክራት ወይም ደግሞ ተንኮለኛ ሆኖ አይወለድም። የአንድ ልጅ የወደፊት አስተሳሰብና ድርጊት አብዛኛውን ጊዜ ሊወሰን የሚችለው እስከ አምስት ዐመት ዕድሜ ባለበት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የፔዳጎጊክ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። ይህ ማለት አንድ ልጅ እስከ አምስት ዐመት ባለ ዕድሜው ውስጥ ከተንኮል ወይም ከመጥፎ ሁኔታዎች ጋር ካደገ ይህን ልጅ በልዩ ዘዴ ካልሆነ በስተቀር ማቃናት እንደማይቻል ይነገራል። ለዚህ ብዙ ሰዎች የፈለገውን ያህል ቢያነቡም አንድ መጥፎ አስተሳሰብ ጭንቅላታቸው ውስጥ ከተቀረጸ በምንም ዐይነት ከመጥፎ ተግባርም ሆነ ከተንኮል ሊላቀቁ አይችሉም። ተንኮላዊ ተግባራቸው በተለያየ መልክ ሲገለጽ ይታያል። እንደዚህ ዐይነት ሰዎች በተለይም ስልጣን ሲጨብጡ የበለጠ ተጠራጣሪዎችና ፈሪዎች በመሆን እራሳቸውን በመውደድና ራሳቸውን ለማዳን ሲሉ ማንኛወም ጭካኔ ተግባር ከመውሰድ አይቆጠቡም። ባጭሩ ስለፖለቲካ በምናወራበት ጊዜ ስለግለሰቦች የህይወት ታሪክም ሆነ የትምህርት አቀሳሰም ዘዴና የሚከተሉትን ፍልስፍና በደንብ ማወቅ አለብን ማለት ነው።

በአውሮፓ የፍልስፍናና የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የአርስቲቶለስ አመለካከት አሸናፊትን በመያዝ በተለይም በሶሻል ሳይንስ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር የትምህርት ይዞታዎች ይበልጥ አርስቲቶላዊ ይዘት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተችሏል። የዚህ አመለካከት በአሸናፊነት መውጣት ከአስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የተከሰተውን የኃይል አሰላለፍ ለውጥና በተለይም የእንግሊዝ ፈላስፎች የፕላቶንን አመለካከት ለመቅበር ያደረጉትን ያልተቆጠበ ትግል ያመለክታል። በሌላ አነጋገር ማንኛውም ግለሰብ በአፈጣጠሩ ስግብግብ ስለሆነ ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ሲል ድርጊቱ ሁሉ በዚህ ጥቅም አሳዳጅነት ይወሰናል በማለት የሰውን ልጅ አርቆ የማሰብ ኃይል ሚና ግምት ውስጥ የማይከት ተቀባይነት እያገኘ መጣ። ይህ በምናያቸው ነገሮች ላይ ብቻ የተገነባ የዕውቀት ምንጭ ቀስ በቀስ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ በመያዝ የጥቂት ሃገሮችን የበላይነት እያሰመረ ሊመጣ ቻለ። በተለይም ህግ ፣ የህብረተሰብ ሳይንስና ኢኮኖሚክስ በዚህ አሪስቶትሊያዊ ፍልስፍናና በኒውተን ሳይንስ ላይ በመመርኮዝ በዓለም ላይ የሰው ልጅ አስተሳሰብ እንዲመረዝና ጥቂት ሃገሮች በብዙ ሃገሮች ላይ የበላይነትን እንዲያሰፍኑና እንዲበዘብዙ አስቻላቸው። በተለይም የኢኮኖሚክስ ትምህርት ከፈጠራ ስራና ዕውነተኛ ዕውቀትን አካብቶ ህብረተሰብአዊ ሀብትን ከማዳበር ተነጥሎ እንዲታይ ሻጥር በመስራቱ ብዙ የሶስተኛው ዓለም ሃገሮች የዚህ ብዝበዛን አምጭና አደንቁሮ አስቀሪ ትምህርት ሰለባ ሊሆኑ በቁ። ጥበብን ፣ ቆንጆ ቆንጆ የህንፃ ስራዎችን ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የሚመኙ መሆናቸው ቀርቶ ድህነትን ፈልፋይ ሆኑ። የዓለም ኮሙኒቲ እየተባለ ለሚጠራው ተገዢ ሆኑ ። በዚህ እጅግ ድብቅ በሆነ ሴራ ብዙ ህዝቦች የራሳቸው ዕድል ወሳኝ መሆን ተሳናቸው። ተመጽዋችና ተሰዳጅ ሆኑ። በተወሳሰበ የጸጥታ የመጨቆኛ መሳሪያ እየተረገጡ ነፃነታቸውን ተገፈፉ። ይህንን የእንግሊዞችን ዕውቀት ምንጭ የተቃወሙት እንደነ ላይብኒዝና ፍሪድሪሽ ሊስት አደገኛነቱን በማሳየት ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ዓለምአቀፋዊ ባህርይ እየያዘ ከመጣ ዓለም በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ እንደምትገኝና የሰው ልጅም ዕድል እንደሚጨልምና ስልጣኔም እንደሚወድም አሳስበዋል። ዛሬ የምናየውን በግሎባላይዜሽን ስም የሚካሄደውን ጦርነትና የሀብት ዘረፋ እንዲሁም ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀሎች መመልከቱ ይበቃል።

ባጭሩ ስለ ዓለም ህብረተሰብ ውዝግብ ፣ስለ ጦርነትና ድህነት በምናወራበት ጊዜ የሰዎችን በተለይም የገዢ መደቦችን የመንፈስ ሁኔታ ፣ አስተዳደግና የዕውቀት ሁኔታ ስሌት ውስጥ ማስገባት አለብን። ስለ ዲሞክራሲ መኖርና አለመኖር ስናወራም ከግለሰቦች የመንፈስ ዕድገትና ጥንካሬ እንዲሁም በራሳቸው ላይ ካለው መተማመን ጋር ማያያዝ መቻል አለብን። ይህንን ስናደርግና በተለይም ደግሞ የህብረተሰቡን የማቴሪያልና የባህል ሁኔታ እንዲሁም የሰፈነውን ዕውቀት ፍርድ ውስጥ ስናዝገባ ስለአንድ የገዢ መደብ ድርጊትና አፍራሽነት ሚዛንና ፍርድ መስጠት እንችላለን ማለት ነው። የኛም ዲሞክራትነትና ዕውነተኛ ስልጣኔ ፈላጊነት ሊወሰን የሚችለው የሌላውን ፀረ-ሞክረሲነት እየደጋገምን ስላነሳንና ሌላውን ስለወነጀልን አይደለም። የኛ ዲሞክራትነት ሊገለጽ የሚችለውና ለህብረተሰብአችንም መፍትሄ መስጠት የምንችለው የነገሮችን አመጣጥ ከሳይንስና ከፍልስፍና አንፃር መመርመርና ማመዛዘን ስንችል ብቻ ነው። ካለበለዚያ አደባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሰ ነው የሚሆነው።

## <u>የዛሬው የህበረተሰብአችን ቀውስ የባህል ችግር ነው!!</u>

በኢትዮጵያ የምሁር እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ የተሰራው ትልቁ ስህተት ከአውሮፓው ስልጣኔ ምንጭ ጋር በደንብ ለመተዋወቅ ጥረት አለማድረግና እንደ አንዳንድ

ሃገሮች የግሪኩን ፍልስፍናና ሳይንስ ወደ አማርኛ ቋንቋ እየተረጎሙ ህብረተሰቡን ለማስተማርና ዕውነተኛ ኤሊት ለማፍራት ያለመቻል ነው። እንዲያውም ለብዞዎች በካፒታሊዝምና በዕውነተኛው የአውሮፓው ስልጣኔ መሀከል ልዩነት እንዳለ ፣ ኩዛኑስ ፣ ላይብኒዝ ፣ ሺለርና ጎይተ ስለህብረተሰብ ዕድገትና ስለስልጣኔ የነበራቸው ግምት ዛሬ ከምናየው ሁኔታ ፍጹም የተለየ መሆኑን ግልጽ አይደለም። እነዚህ ታላላቅ ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች ስለህብረተሰብ ዕድገት ሲመራመሩ ጥበባዊ(aesthetic) የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ዋናው የስልጣኔ መመሪያ አድርገው ነው። ጥበባዊ መንግስትና ጥበብ የተሞላበት ህብረተሰብ የአንድ ህዝብ መመሪያ እንደሆነ ያስተምራሉ። ስለዚህም ነው ዛሬ የምናያቸው በጠቅላላው በማዕከለኛው ዘመን የተመሰረቱትና የተገነቡት ከተማዎችና የዳበሩት የዕደ-ጥበብ ስራዎች ይህንን የክላሲካል ፈላስፎችን መመሪያ በማደረጋቸው ነው። እንደነ ማስትሪችና አንትቨርፐን የመሳሰሉት ታይተው የማይጠገቡ ከተማዎችና በተለያዩ የአውሮፓ ሃገሮች የምናያቸው ካቴድራሎች የተሰሩት በተራ ዕውቀት ሳይሆን ራስን በማስጨነቅና ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ስምምነትን ለማምጣት ከመፈለግ የተነሳ ነው። በዩኒቨርስ ህግ መሰረት የሰው ልጅም አኗኗር የተስተካከለና ጥበባዊ መሆን አለበት። ይህንን የዩኒቨርስ ህግ የሚጥስ ሁሉ ጭንቅላቱ ተዘበራርቆ ህብረተሰቡም ልቅ እንዲሆንና ጉዞው ወዴት እንደሆነ እንዳያውቅ ይደረጋል። ዛሬ የምንማረው በየትምህርት ቤቱና በየዩኒቨርሲቲ የሚሰጠው ትምህርት ይህንን የዩኒቨርስ ውስጣዊ ህግ የጣሰ ነው። ተፈጥሮን ተበዝባዥና እንዲናጋ የሚያደርግ ነው። የሰው ልጅ እንዳለ ነገ ይሞት ይመስል በመጣደፍ የተፈጥሮን ሀብት እየበዘበዘና ሚዛኑን እያናጋ እንዲኖር በዚህም ራሱ የተፈጥሮ አደጋ ሰለባ እንዲሆን የሚያደርግ የትምህርት ዐይነት ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ ***የዛሬው የካፒታሊዝም ዕድገትና "ስልጣኔ" የኒዎ ሊበራል ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉን የገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና ውጤት ሳይሆን ፣ በሳይንስ ላይ የተመሰረተ የከፍተኛ ዕወቀት ውጤት ነው። ከዚህ ውጭ ማየት ስለ ዕውነተኛ ዕድገትና ስልጣኔ ግንዛቤ እንዳይኖር ትግል ማደረግ ነው።***

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ በተለይም የተማሪው እንቅስቃሴ እያየለ መምጣቱና ማርክሲዝምን እንደ መታገያና እንደ ህብረተሰብ መተንተኛ ዘዴ መጠቀሙ ለጊዜው አማራጭ የሌለው ሆኖ ቢታይም ፣ የማርክሲዝም አተረጓጎም ተጣሞ በመግባቱ የህብረተሰብአችንን አወቃቀርና የማቴሪያል ሁኔታ በቅጡ መረዳት አልተቻለም። ለምሳሌ የማርክስን የተለያዩ ስራዎች በደንብ ያነበበ ማንኛውም ህብረተሰብ በቀጥታ ከፕሪሚተቭ ኮሙኒዝም ወደ ባርያና ወደ ፊዩዳሊዝም ከዚያም ወደ ካፒታሊዝም እንዳልተሸጋገረ መረዳት ይቻላል። በሌላ አነጋገር ማርክስ ለማሳየት እንደሞከረው አንድ ህብረተሰብ አንድ ወጥ እንዳልሆነና የተለያዩ የአመራረት ስልቶችና ህብረተሰብአዊ ግኑኝነቶች ተጣምረውና ተዘበራርቀው እንደሚገኙ ነው። ስለዚህም ስለአንድ ህብረተሰብ ዕድገትም ሆነ ፀረ-ዕድገት አንድ ነገር ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ሁኔታዎች በመሰበጣጠር ዕድሉን ሊወስኑ ይችላሉ ማለት ነው። በሌላ ወገን ደግሞ በማርክስ አቀራረብ የማቴሪያል ሁኔታዎች የአንድን ህብረተሰብም ሆነ ፖለቲካ ስልጣንን የጨበጠ የማሰብ ኃይልን ይወስናል የሚለው አቀራረብ ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ተደርጎ በመወሰዱ ፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሰፈነውን የሀብት ክፍፍል በመለወጥ የሰውንም አስተሳሰብ መለወጥ ይቻላል የሚለው ጭንቅላት ውስጥ ስለተቀረጸ ይህ ጉዳይ ወደ ማይሆን ውዝግብ ውስጥ እንድንገባ አድርጓል። በተለይም ማርክስ ከነሶክራቶስና ከፕላቶን ፍልስፍና ተላቆ ማቴሪያለሲ አቋም መውሰዱና የካፒታሊዝም ቲዎሪ በአዲስ መልክ መጻፉ ፣ የማርክሲዝምን አርማ ይዘው የሚታገሉ ግለሰቦችንንም ሆነ ድርጅቶችን አንድ ህብረተሰብ ዘለዓለማዊ የመደብ ትግል የሚደረግበት መድረክ ነው ወደ ሚለው እንዲያዘነብሉ አድርጓቸዋል። ይህ ማለት ደግሞ የመደብ ትግሉ በአመጽ ነው ሊፈታ የሚችለው ወደ ሚለው ድምደማ ላይ ያደርሰናል። በሌላ ወገን ግን ማርክስ ስለካፒታሊዝም ውስጣዊ ክንዋኔ የሰጠው የኢኮኖሚ ትንታኔ ከሌሎች የክላሲካል ኢኮኖሚስቶች ጋርም ሆነ ከኒዎ ሊበራል አኮኖሚስት ቲዎሪዎች ጋር ሲወዳደር በጣም የተሻለ ብቻ ሳይሆን ካፒታሊዝም እንዴት እንደሚሰራ በደንብ ያሰቀምጣል። ሶስቱን የማርክስ ዳስ ካፒታል ላነበበ ፣ ማርክስ ለማሳየት የሞከረው የካፒታሊዝምን ዕድገት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ መምጣት ፣ ለፍጆታ በሚውልና ለትርፍ ተብሎ በሚመረት መሀከል ስላለው ስለ አንድ ዕቅ ቅራኔ ፣ ወዝአደሩ ራሱ የዋጋም ሆነ የትርፍ አመንጪ ስለመሆኑና ፣ ወለድና ፣(interest) ኪራይ(rent) ከትርፍ እንደሚመነጩ የሚያመለክት ነው። በማርክስም ትንተና ውድድርና ገንዘብና የኬሬዲት ስርዓት ለካፒታሊዝም ዕድገት ዋናው አንቀሳቃሽ ኃይሎች ናቸው። የማርክስ ኢኮኖሚክስ በተለያዩ መስኮች ዘንድ ያለውን ውስጣዊ ግኑኝነትና የንግድ ልውውት ሲያመለክት በተማያቋርጥ የቴክኖሎጂ ዕድገት አጠቃላይ የካፒታሊስት የሀብት ክምች እንደሚፈጠር ሲያመለክት ፣ በሌላ በኩል በቴክኖሎጂ ፈጣን ዕድገት ምክንያት የተነሳ ሰራተኛው በቴክኖሎጂ እየተተካና ትርፍ እንደሚቀንስ ያመለክታል። ይሁንና የማርክሲዝም ቲዎሪ አንድ ህብረተሰብ እንዴት እንደሚሰለጥን በፍጹም አያሳይም። ምክንያቱም ማርክስ ስለተፈጥሮ ሳይንስ አስፈላጊነት

ስለከተማዎች ግንባታና ስለ አንድ ህብረተሰብ ጥበባዊ ግንባታ የጻፈው ስለሌለ ነው። በዚህ ምክንያት በብዙ የሶስተኛው ዓለም ሃገሮች የተደረጉት አብዮቶች በሙሉ ሊጨናገፉና ለህብረተሰብአቸው የተፈለገውን ውጤት ሊያመጡ ያልቻሉት።

እንደሚታወቀው የማርክስ ተዎሪ ሙሉ በሙሉ ባደገ የካፒታሊዝም ህብረተሰብ ውስጥ የተፈጠረ ቢሆንም ተግባራዊ ለመሆን የተሞከረው በማቴሪያልም ሆነ በአስተሳሰባቸው ወደ ኋላ በቀሩ ሃገሮች ነው። እነዚህ ሁለት ተጻራሪ ሁኔታዎች ሲገናኙ ጭንቅላትን ከማጽዳትና ዲሞክራት ከማድረግ ይልቅ ቲዎሪው ወደ ፖለቲካ ቲዎሪና ወደ ስልጣን መያዣ በመተርጎሙ ሳይወድ በግድ ወደ ውስጥ ህብረተሰብአዊ አፈናና የማታሪያል ሁኔታዎች በተለይም የምርት ኃይሎች ተፍታተው እንዳያድጉ ማፈን ችሏል ማለት ነው። የማርክስ ዳስ ካፒታል ደግሞ የሚያሳየው ይህንን የሚጻረር ፣ የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ከተራ የሸቀጣ ሸቀጥ ኢኮኖሚ ወደ ተወሳሰበና ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እንደሚያመራ ነው። በሌላ አነጋገር ውስጣዊ የተፈጥሮ ህግ አለው ማለት ነው። ይህንን መረዳት ሲቻል ካፒታሊዝም ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን መገንዘብ ይቻላል።

ወደ ሃገራችን ስንመጣ የተፈጠረው ችግር ከዚህ በአንድ በኩል ከግሪኩ ስልጣኔ ጋር ለመተዋወቅ አለመፈለግ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ማርክሲዝምን በደንብ አብላልቶ ውይይት ሳይደረግበት የህብረተሰብ ችግር መፍቻ አድርጎ መውሰድና ወደ ግብግብ ውስጥ መግባት። እዚህ ላይ ዛሬ አንዳንድ ዶኩሜንቶችን ስንመረምር በጊዜው የጠለቀ ዕውቀት ያላቸው ግለሰቦችና አስተማሪዎች ቢኖሩም በኋላ እየተካለበ የመጣው የተማሪ እንቅስቃሴ ክፍል ነገሮችን ማጣመምና በተለይም የብሄረ-ሰብ እንቅስቃሴና የብሄረ-ሰብ ጭቆና ለሚለው ጭንቅላትን ለሚጋርድ ትግል መስመሩ ልቅ እንዲሆን በማድረግ ወደ ማይሆን ሽኩቻ ውስጥ ሊያስገባ በቅቷል። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠረው ውዝግብና ውንብድና የተሞላበት ትግል ጠቅላላው የተማሪው እንቅስቃሴ ተጠያቂ አልነበረም። በዚህ ላይ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አወቃቀርና በህብረተሰብአችን ታሪክ ውስጥ ምንም ዐይነት ሳይንሳዊ ውይይትና የፍልስፍና ክርክር አለመኖሩ ፣ በተለይም የኑሮ ትርጉም ምንድነው? ፣ የሰው ልጅ ለምን በዚህ ዓለም ላይ ይኖራል? ፣ ከተፈጥሮስ ጋር የሚኖረው ግኑኝነት ምንድነው? በተፈጥሮ ውስጥ ያሉትን ጥሬ-ሀብቶች እንዴት እያወጣ መጠቀም ይችላል? ኑሮውንስ በምን ዘዴ ያሻሽላል? ከተማዎችንስ እንዴት ይገነባል? የሚሉት መሰረተ ሃሳቦች ውይይት ሊደረግባቸው ዕድል ባለማግኘታቸውና የህብረተሰብም ክፍልም ስላልነበረ በካፒታሊዝም አፍላ የተፈጠረው ምሁር በሰፊውና ህብረ-ብሄርን በመገንባትና ህብረተሰብን በማዋቀርና በማጠንከር ላይ ሊሰማራ አልቻለም። በሌላ አነጋገር በተለያዩ ጊዜ የተነሱ የገዢ መደቦች በተለይም አፄ ኃይለስላሴ ለኢትዮጵያ ወደ ኋላ መቅረትና የህብረተብአችንን ዕድገት ሊያጣምም የሚችል የቴክኖክራት መደብ ብቅ እንዲል የበኩላቸውን አስተዋጽዎ አድርገዋል ማለት ነው። በሳቸው አማካይነት የገባው ቁንጽል ዕድገትና የትምህርት ስርዓት በአስተሳሰቡ የተጣመመና ተንኮለኛ እንዲሁም ደግሞ በራሱ ላይ ዕምነት የሌለው የህብረተሰብ ክፍል ብቅ አስችሏል።

እነዚህን ነገሮች ላይ ከሰፈረው የፍልስፍናና የህሊና ሳይንስ ጋር እያነጻጸርን እንመልከት። ብዙ ጊዜ ከኢትዮጵያ ግራዎች ስለ ኢትዮጵያ ፊዩዳሊዝም በሚጻፍበት ወይም በሚወራበት ጊዜ ብዙዎች ይህንን አባባል የሚቃወሙት እንደስድብ አድረገው ነው። ፊዩዳሊዝም የሚለው ጽንሰ-ሃሳብና ስነ-ስርዓት በአውሮፓ የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የነበረና በማርክሲዝምም ሆነ በከበርቴው ታሪክ ጸሀፊዎች ዘንድ ስምምነት እንደነበረና ለህብረተሰብም ዕድገት ዕንቅፋት እንደሆነ የታመነበት ጉዳይ ነው። የእነ አዳም ስሚዝን የነጻ ገበያ ቲዎሪ ላነበበ በአንድ በኩል ፊዩዳሊዝምን የሚዋጋ ( see the corn Law) በሌላ በኩል ደግሞ በመርካንታሊዝም የሚደገፈውን በመንግስት አማካይነት የሚካሄደውን የማኑፋክቱር ፖሊሲ የሚቃወምና ሙሉ በሙሉ በውድድር ካፒታሊዝም ላይ እንዲካሄድ ትግል የሚደረግ ነበር። በሌላ አነጋገር እነ አዳም ስሚዝና ሪካርዶ ፀረ-ፊዩዳል ምሁሮች ነበሩ። በ1960ዎቹ ዓመታት በሰፊው በማርክሲስት የታሪክና የኢኮኖሚ ምሁሮች ዘንድ የተካሄደውን በአውሮፓ ውስጥ የፊውዳሊዝምን ወደ ካፒታሊዝም ህብረተሰብ መሸጋገር ክርክር ላዳመጠ( the transformation debate) ውይይቱ የተወሳሰበ ብቻ ሳይሆን በቀላሉ ሊፈታ ያልቻለ ነው። ከክርክሩ መረዳትም እንደሚቻለው በአውሮፓ ውስጥ የካፒታሊዝም ዕደገት ብዙ ክንውኖችን ያካሄደና ቀስ በቀስ እየረጋ እንደመጣ ነው። ይህ የማርክሲስቶችና የአንዳንድ ከበርቴያዊ አስተሳሰብ ያላቸው የታሪክ ምሁሮች ውይይት በተለይም ከዘመነ ሬናንሳ በኋላ ብቅ ያለውን የጭንቅላት ተሃድሶ የአስተሳሰብ ስልት ለውጥ ከትንተና ውስጥ አላገባም።

ወደ ሃገራችን ስንመጣ አብዛኛውን ጊዜ የተማሪውን ማህበር የሚወነጅሉት ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች ይህ ፊዩዳሊዝም የሚለው ነገር ባይነሳ ኑሮ እያሉና ከሃማሳኛው ዓመታትም ሆነ በኋላ የነበረው የህብረተሰብ አወቃቀር ማርና ወተት የሚፈስበት ሃገር እንደነበረና ይህ ዐይነቱ የተሳሳተ አመለካከት ግንዛቤ ውስጥ በመግባቱ ነው። በሃምሳኛውና በስድሳኛው ዓመተ ምህረቶች የነበረውን የሃገራችንን ዕድገትና የኑሮ ሁኔታ ለመረዳት ለማይፈልጉ ከውጭ በመጣ ፍልስፍና ሃገራችን አቅጣጫዋን እንድትስት ተደርጋለች እየተባለ በፍጹም ከታሪክና ከሳይንስ ጋር ያልተገናዘበ ወሬ በመወራት ብዙዎች እንዲሳሳቱና ዕውነትን ከውሸት እንዳይለዩ ለማድረግ በቅቷል። በተለይም ከኢጣሊያን መባረርና ኢትዮጵያ ነጻነቷን ከተቀዳጀች በኋላ የተወሰዱት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የፊዩዳሉን ስርዓት በልዩ መልክ የሚያጠናክሩና ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተሰበጣጠረ በገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ የተኮላሸ የካፒታሊዝም ስልተ-ምርት በመስፋፋት ውስን በሆነ መልክ ብቻ ኢኮኖሚ ዕድገት እንዳመጣ ለብዙዎቹ ግልጽ አልነበረም። ይህ ታስቦበትና ተጠንቶ ያልተካሄደ የዘመናዊነት ፖሊሲ በህብረተሰብ ውስጥ ልዩ ቅራኔ በመፍጠር ፣ ህብረተሰብ ውስጥ አዲስና ውስጠ-ኃይሉ ከፍ ያለ የህብረተሰብ ክፍል እንዳይወጣ አገደው። በሌላ ወገን ደግሞ የፊዩዳሊዝም የማቴሪያል ሁኔታና ብዝበዛ ተጋኖ በመወሰዱ ኋላ ለተከሰተው አመጽ ምክንያት ሊሆን ችሏል። ለምሳሌ የአውሮፓን ፊዩዳሊዝም ከኢትዮጵያው ጋር ለወዳደረ ፣ የአውሮፓው ገበሬውን እንደራሱ ዕቃ አድርጎ እስከመውሰድ ድረሰና ብዝበዛውንም ያጠናከረ ስለነበረ ብዙውን ጊዜ የገበሬዎች ማመጽ በየቦታው እንደተከሰተና ለመብታቸውም ይታገሉ እንደነበር ተመዝግቦ ይገኛል። በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያው ፊዩዳሊዝም በዝባዥነት እጅግ ተጋኖ የቀረበና የፊዩዳሉን የኑሩ ሁኔታ ትንተና ውስጥ ያላገባ ነበር። በብዙ ቦታዎች በፊዩዳሉ መደብና በገበሬው መሀከል በምግብ ዐይነት አበላል ልዩነት ከመኖሩ በስተቀር በሌላው የኑሮ ሁኔታ ይህንን ያህልም የተሻለ አልነበረም።

እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ፊዩዳሊዝም ከሜታፊዚክስ አንጻር በሰዎች የማሰብ ኃይል ላይ ያለውን ተጽዕኖ አስመልክቶ የተጻፈ ጽሁፍም ሁነ የህሊና ሳይንስ ምርምር የለም። በደፈናው ከሁሉም አቅጣጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በአፈጣጠሩ ከሌላው የተለየ ይመስል ልዩ ባህል እንዳለውና ይህም የስልጣኔው ምልክት እንደሆነ እስካሁን ድረስ ይወራል። እንደዚህ ተብሎ ሲወራ ደግሞ ባህል በአንድ ቦታ ላይ የቆመና የማይለዋወጥ ፣ እንዲሁም ደግሞ በከተማዎች ዕድገት ፣ በአርኪቴክቸር ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የማይገለጽ በልብስና በአበላል ወይም በምግብ ብቻ የሚገለጽ የሚመስላቸው አሉ። በተለይም የኢትዮጵያ ታሪክ አጻጻፍ በፓንክህረስት በመያዙና ይህም የአጻጻፍ ስልት መመሪያ በመሆኑ ሁላችንም በዕውነተኛ ስልጣኔ በማይገለጸው እየተዝናናንና እየኮራን እንድንኖር ተገደናል።

በአውሮፓ የእስተራረስ ታሪክ ውስጥ በማዕከለኛው ክፍለ-ዘመን ለምሳሌ የዕደ-ጥበብ ስራዎችም ሆነ የአስተራረስ ዘዴዎች እየተሻሻሉ ሲመጡ የኢትዮጵያ ገበሬ ለዘመናት በወገልና በማረሻ እንዲሁም በበሬ ብቻ እየታገዘ ነው ያርስ የነበረው። አውሮፓ ውስጥ በበሬ ማረስ ይህንን ያህልም ውጤት ማምጣት እንደማይቻል የተረዱት ገበሬዎች በፈረስና በተሻለ ቴክኒክ ማረስ ሲጀምሩና የምርታቸውን ውጤት ሲያሻሽሉ እኛ ግን እዛው ባለንበት በመርጋት ለችግርና ለረሀብ ተዳርገናል። የሶስት ዐይነት እርሻ ዘዴዎች የሚባሉት የተለያዩ የሰብል ዐይነቶችን በተለያዩ ወራት መጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ የተስፋፋ አልነበረም። በአውሮፓ ግን እየተስፋፋ የመጣና ይህ የአስተራረስ ስልት ለምርት ዕድገት አመቺ ሁኔታን እንደፈጠረ የታመነበት ጉዳይ ነው። የአውሮፓው ፊዩዳሊዝም የራሱን በተለያዩ መስኮች የራሱን መቃብር ሲቆፍርና በውጭ ንግድ አማካይነትና በዕዳ ሲቦረቦር የኛው ግን የተዘጋ ነበር። በተጨማሪም ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ በስተቀር አብዛኛዎች የፊዩዳል ግኑኝነት አልነበራቸውም። የጋዳ ታሪክ አለን እያሉ የሚያሰጨንቁንን አንዳንድ የኦሮሞ ታጋዮች በታሪካቸው ውስጥ በአንድ ቦታ ረግቶ በመቀመጥ የስራ ክፍፍልን የማዳበር ባህል አልነበራቸውም። ከነሱ በተሻለ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙት የንጉስ አገዛዝ የነበራቸው የከምባታ ፣ የሀድያና የከፋ አገዛዞች ናቸው። ከኦሮሞዎች ይልቅ በነዚህ አካባቢ የምርት መሳሪያዎች ሁኔታና ዕድገት የተሻለ ነበር ብሎ መናገር ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ተባለ ከዕውነተኛ ስልጣኔ አንጻር ጠቅላላው የኢትዮጵያ ግዛት የሚያዝናና የስራ ክፍፍል የዳበረበት ነበር ብሎ መናገር አይቻልም። እስከ አስራዘጠናኛው ክፍለዘመን መጨረሻ ድረስ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ባለህበት የረጋ ፣ በማቴሪያል ሁኔታው የደቀቀ ፣ ለስራ ክፍፍል በር መክፍት ያለቻለ ፣የዕደ-ጥበብ ስራዎችና ንግድ እንደ አጸያፊ ሙያዎች የሚታይበትና በህበረተሰቡ ውስጥ ህብረተሰብአዊ እንቅስቃሴ(social mobility) የማይታይበት ነበር። በዚህ ላይ መፈናፈኛ የሌለውና ከፍልስፍና ጋር ምንም ግኑኝነት ሊመሰርት ያልቻለው የኢትዮጵያ ሀይማኖት የህዝቡን አስተሳሰብ አፍኖ በመያዝ የራሱን ዕድል በራሱ

እንዳይወስን ማድረግ ችሏል። ይህ አጠቃላይ ሁኔታ ጠቅላላው ህብረተሰብ እርስ በርሱ የነበረውን ግኑኝነት ሲወሰን ፣ በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን ሀብት እያወጣ እንዳይጠቀምና የስልጣኔ ባለቤት እንዳይሆን አገደው። በተለይም በፊዩዳሊዝም የአኗኗር ስልት የብዙ መቶ ዐመታት ታሪክ ያለውን የሰሜኑን ኢትዮጵያ ክፍል ለተመለከተ የፊዩዳሉ ባህል ከሃይማኖት ጋር በመጣመር የህብረተሰቡን የስራ ክፍፍል እዚያው በዚያው ቀልፎ እንደያዘው መረዳት እንችላለን። ይህ ብቻ አይደለም። ይህ የማሰብ ኃይል አለመዳበር ፣ ተፈጥሮን መቃኘት አለመቻልና ተፈጥሮን ጓደኛ ለማድረግ ብቃት አለመኖር ህብረተሰቡ በተፈጥሮ ላይ ዘመቻ እንዲያደርግ አስገደደው። መሬትንና ዛፍን መንከባከብ ፣ ትንንሽ የመስኖ ስራዎችን ማስፋፋትና የመሬቱን የወሀ መቋጠር ኃይል ማሻሻል የተለመደ ባለመሆኑ ተፈጥሮን ወደ ተራ የተብዝባዥነት ሁኔታ ውስጥ በመክተት የመሬቱ ለምለምነት እንዲወድምና ወደ ድርቅነት እንዲለወጥ አደረገ። ይህ ተፈጥሮን የመንከባከብ ባህል አለመኖር ፣ የእርሻን ተግባር ማሻሻል መዳበር አለመቻል ፣ በተወሰኑ ሰብሎች ላይ ብቻ ማትኮርና ያሉትን ሰብሎችና የከብት ውጤቶች በልዩ ልዩ መልክ እያመረቱ ማቅረብ ያለመቻል የህብረተሰቡ የአኗኗር ስልት በመሆን እስከዛሬ ድረስ በረሀብና በድህነት እንዲደቅ ሆኗል። በኋላ እየተፈጠረ ስለመጣው ድርጊታችንና አስተሳሰባችን በምናወራበት ጊዜ ይህንን ሀቅ መሳት አንችልም። ብዙ የህብረተሰብና የህሊና ሳይንስ ምርምሮች እንደሚያመለክቱት በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተለመዱ ባህሎችና የአኗኗር ስልቶች ለብዙ መቶ ዐመታት መቆየት እንደሚችሉ ነው። ይህንን ካለብዙ ምርምርም መመልከትና መረዳት ይቻላል። ዛሬ በሃገራችን ብቻ ሳይሆን በሌሎች የሶስተኛው ዓለም ሃገሮችም ያለው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ ለተመለከተ የድሮ የአስተሳሰብ ባህሎች ከአዲሱ መንፈስን ማደስ ከማይችለው ባህል ጋር ሲጋጩ ጥሩ ውጤት ከማሳየት ይልቅ የየህበረተሰቡን የማሰብ ኃይል በማኮላሸት ታሪካዊ ስራዎችን እንዳየሰራ እንደሚያግዱት ነው።

ወደ ሃገራችን ስንመጣ የካፒታሊዝም መግባትና በሞኔተሪ መልክ የኢኮኖሚው ዕድገት መገለጽ በተለይም በአስተሳሰቡ የዳበረ ሳይሆን ፣ ልዩና ሃገርን የሚሰረስር እንዲሁም ሰፊውን የህብረተሰብ ክፍል የሚንቅ ኃይል በአማዛኝ ጎኑ ብቅ ብሎ እንዲወጣ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል። በሌላ አነጋገር የካፒታሊዝም ወደ ሃገራችን መግባት እንደተባለው የመንፈስ ተሀድሶና እርቆ የማሰብ ኃይል ያለው ህብረተሰቡን ሊመራ የሚችል የህብረተሰብ ክፍል ብቅ እንዲል በፍጹም አላገዘም። ይህ በፍጆታ አጠቃቀሙና በአረማመዱ ከህብረተሰቡ እየተነጠለ የመጣ የህብረተዘሰብ ክፍል በአስተሳሰቡ የተዘበራረቀ ፣ ሙልጭልጭ የሚልና ሃገርን በቀላሉ የሚሸጥ ሆነ። የብሄራዊ ነፃነት ትርጉም የማይገባው ፣ አንድ ህብረተሰብ እንደ ህብረተሰብ እንዴት መዋቀር እንዳለበት የማይገነዘብ ፣ የዱር አዳሪ የሚመስል የህብረተሰብ ክፍል እዚህና እዚያ ብቅ በማለት የህብረተሰቡን የማሰብ ኃይል ማኮላሸት ብቻ ሳይሆን የሃገሪቱን ዕድገት አቅጣጫ በማሳት የተወሳሰቡ የህብረተሰብ ቅራኔዎችና ችግሮች እንዲከሰቱ በማደረግ ልንወጣው የማንችለው ማጥ ውስጥ ጥሎን ሄደ። በተለይም በአፄ ኃይለስላሴና አገዛዛቸው ብዙም ሳይታስብበት ከምዕራቡ ዓለም እየተቆራረጠ የገባው የትምህርት ስርዓት ስብአዊነትንና ዕድገትን የሚያመጣ መሆኑ ቀርቶ በኋላ በአብዮቱ ዘመን እንደተከሰተው እጅግ አረመኔያዊ የተሞላበት ድርጊትም ሊፈጽም የሚያስችል ሁኔታ ሳያውቀው ከጭንቅላቱ ጋር እያዋሀደ መጣ። የአሜሪካን ኢምፔሪያለዝም ተጽዕኖ እያየለ ሲመጣና የሚሊታሪው ፣ የጸጥታውና የሲቢል ቢሮክራሲው በአሜሪካንና በአንዳንድ የምዕራብ አገሮች የአሰለጣጠን ዘዴ ሲሰለጥን ፣ በአንድ በኩል የመንግስቱ መኪና ታሪካዊ ተግባሩን እንዳያካሂድ ወደ መጨቆኛነት ሲሸጋገር ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ይህ በሚሊታሪውና በሲቢል ቢሮክራሲው ወስጥ ተሰግስጎ ታሪክን እንዳይሰራ የተኮላሸው የህብረተሰብ ክፍል ዕድሉን ከአሜሪካን ኤምፔሪያሊዝም ጋር በማድረግ የሃገሪቱን ዕድግትና ብሄራዊ-ነፃነት መቀናቀን ጀመረ። ኢትዮጵያ ወዴት እንደምታመራ ፣ ህዝቡ ምን እንሚፈልግና ምንስ እንደሚያሰፈልገው ማውረድና ማውጣት ተሳነው። አዲስ ባገኘው የአኗኗር ስልት ጭንቅላቱ ታወረ።

ይህ የተዘበራረቀ የማቴሪያልና የህሊና አወቃቀር በህበረተሰቡ ውስጥ በተለይም በብሄረ-ሰብ ደረጃ ልዩ ዐይነት ክስተትና ቅራኔ እየያዘ መጣ። የካፒታሊዝም ስልተ-ምርት ህዝቡን ከማቀራረብና የማሰብ አድማሱን ከማስፋት ይልቅ እያራራቀው መጣ። ከዚህ ጋር በአፄ ኃይለስላሴ ብዙም ሳይታሰብበት እንዲስፋፋ የተደረገው የሚሽን ትምህርት በአንዳንድ ቦታዎች ማንነቱን የሳተ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ እንዲል አደረገ። ኢትዮጵያዊነቱን የሚክድ ፣ በራሱ ላይ ዕምነት የሌለው ፣ እንግሊዘኛን ከኦሮምኛ ቋንቋ ጋር እያደባለቀ በመናገር እራሱን ከህብረተሰቡ የሚያገል ኃይል ሆነ። ይህ የህብረተሰብ ክፍል ራሱ ነፃ ሳይወጣና የመንፈስ ተሃድሶ ሳያደርግ ብሄረ-ሰቤን ነፃ አወጣለሁ ወደ ማለት አመራ። ህብረተሰቡ ከመቀራረብ ይልቅ አንዱ ከሌላው የተለየ ይመስል ፣ አንደኛው ብሄረ-ሰብ በሌላው ላይ ጭቆናን የጫነ ይመስል የማይሆን ትርጉም እየተሰጠ የህብረተሰቡ ዋና ችግር

የብሄረ-ሰቦች ችግር ነው እየተባለ ልንወጣ የማንችለው ማጥ ውስጥ እየከተተን መጣ። የታሪክን ሂደት ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮን ህግና ሳይንስን የሚጥስ አስተሳሰብ በመስፋፋቱና ቀስ በቀስም ስር እየሰደደ በመምጣቱ ህብረተሰቡ ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ዕድገት እየተጋለ ያለበትን የማቴሪያልም ሆነ የመንፈስ ችግር እንዳይወጣ ጭንቅላቱ እንዲጋረድ አደረገ። ብሄረ-ሰቤን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተቋቋመው የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት በተለይም ከአንድ አካባቢ የመጡ ወጣቶችን በማሳሳት የሃገራችንን አንድነትና ዕድገት የሚቀናቀን የጥላቻ ቅስቀሳ ጀመረ። የፀረ-ስልጣኔ ህልማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ከዚህም ሆነ ከዚያኛው ድርጅትም ሆነ ሃገር ዕርዳታ በመሰብሰብ ትግላቸው ዓለም አቀፋዊ ባህርይ እንዲኖረው አደረጉ። በጊዜው በድርጅቱ ውስጥ ብዙ የተማሩ ግለሰቦች ቢኖሩም ጠቅላላውን የሃገሪቱን ችግር በተማሩት መነጽር ሊመለከቱና ትንተና እየሰጡ መፍትሄ ሊያቀርቡ አልቻሉም። ራሳቸውን ይበልጥ እያገለሉና ታሪክን እያጣመሙ በውይይትና በመግባባት ሊፈታ የሚችለውን ጥያቄ ውስብስብ አደረጉ። ጥያቄው የቅኝ ግዛት ጥያቄ ሆኖ በመቅረቡ ለሌሎች የኢትዮጵያን አንድነትና ዕድገት ለሚሹና ለዚህም ዓላማ ለሚታገሉ ኃይሎች ሊዋጥ የሚችል ነገር አልነበረም። በሌላ ወገን ደግሞ በአብዮቱ ወቅት አብዮቱን የሚያግዝ ሌላ የኦሮሞ ደርጅት ይቋቋማል። ይህ አንድ ትልቅ እርምጃ ቢሆንም ደርግ እየተዳከመ ሲሄድ በአብዮቱ ዘመን የደርግ ካድሬዎች የነበሩና ለትምህርት ልዩ ልዩ የምስራቅ አውሮፓ ሃገሮች የተላኩ ኦሮሞዎች አንዳንዶቹ ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ ወደ ምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ በመምጣት የኦሮሞን እንቅስቃሴ ይቀላቀላሉ። የተቀሩትም ጨርሰው ከመጡ በኋላ በትግሉ በመካተት የበለጠ በጥላቻ ላይ የተመሰረተውን ትግላቸውን ያጧጧፋሉ። አብዛዎችን በጥሞና ቀርቦ ለመወያየት በፍጹም አይቻልም ነበር። አንዳንዶቹ ደግሞ በአብዮቱ ዘመን የራሳቸውን ስራ ሲሰሩ የነበሩ ስለሆነ ይህ እያስበረገጋቸው ነው መሰለኝ አቀራረባቸው ሁሉ እንደነብር የሚያስፈራ ነበር። ያም ሆነ ይህ በደርጀቱ ውስጥ የመኢሶንና የኢህአፓ እንዲሁም የደርግ ካድሬዎች የነበሩ በመቀላቀል ከዚህ በፊት የቆሙለትን ዓላማ ወደ መካድ ደርሰዋል። ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ ለጊዜው የስልጣን ተካፋይ በመሆን የተፈጠረውን የፖለቲካ ትርምስ በመጠቀም በተለይም በአማራና በጉራጌ ብሄረ-ሰቦች ላይ አሰቃቂ እርምጃ በመውሰድ ለብዙ መቶ ህዝብ ህይወት መጥፋት ተጠያቂ ሊሆኑ በቅተዋል። ዛሬም ያሉበት ችግር ፣ በሰለጠነ ዓለም ውስጥ ቢኖሩም ከዚህ የጥላቻ መንፈስና ሊደረስ የማይችል ህልማቸው ለመላቀቅ አለመቻላቸው ነው። እነሱ ጠፍተው ለልጆቻቸውም የጥላቻ መርዝ በመነስነስ በራሳቸው ላይ ዕምነት እንዳይኖራቸው እያደረጉ ነው። ከዚህ ጭንቅላት ውስጥ ከተተከለ መርዝ እስካልተላቀቁና ያደረጉትንና የሚፈጽሙትን ድርጊት መጠየቅ እስካልቻሉ ድረስ የሚመኙትን በፍጹም ሊያገኙ አይችሉም። በተረፈ ያቺ ሃገር የጠቅላላው ህዝብ ሃገርና በውስጧም ያለው የጥሬ-ሀብት የሁሉም ስለሆነ እነሱ ብቻቸውን የኛ ብቻ ነው ብለው ሌላውን ከንብረቱ ሊያፈናቅሉ አይችሉም። አንድን ህብረተሰብ በእልክና ለብቻ መገንባት የማይቻል መሆኑን ተገንዝበው ከገቡበት አዙሪት ውስጥ በመውጣት ለቀናና ግልጽ ውይይት ዝግጁ መሆን አለባቸው። በዚህ ብቻም የኦሮሞም ሆነ ሌላው ህዝብ የዕውነተኛ ስልጣኔና ነፃነት ባለቤት ሊሆን ይችላል።

ወደ ኤርትራ ጥያቄ ስንመጣ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን የተሰራውን ስህተት ወደ ጎን ትተን ትግላቸው “አተርፍ ባይ አጉዳይ” እንዲሉ በማቴሪያልም ሆነ በሰው ኃይል ብዙ ንብረት የወደመበትና ህይወት የጠፋበት ነው። እንደሚታወቀው ከሌሎች ክፍለ-ሀገሮች ጋር ሲወዳደር ኤርትራ በዕድገት የተሻለና የከተማዎችም ዕድገት ስርዐት ነበረው። ኤርትራውያን በአገዛዙም ሆነ በልዩ ልዩ መስኮች ተሰማርተው ከፍተኛ ጥቅም የሚያገኙ ነበር እንጂ በዚህ መልክ ተጨቁነናል ብለው ወደ ጦር ትግል የሚያሰኬዳቸው ምንም ነገር አልነበረም። ትግሉን እያፋፋሙ ሲመጡ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ እያጠነከሩ መጡ። በተለይም ወጣቱን በመመረዝ ሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲንቅ አደረጉ። እነሱ የሰለጠኑ ሌላው ደግሞ ወደ ኋላ የቀረ ነው እያሉ ወጣቱን የማይሆን የውሸት መርዝ ነሰነሱበት። በሌላ በኩል ደግሞ እንደዚህ ሰልጥነናል ብለው የሚያወሩትን ያህል የሚዘገንን ተግባር እየፈጸሙ መጡ። በተጨማሪም አማራው ብሄረ-ሰብ ጭራቅ ነው ተብሎ ለወጣቱ በመነገሩ ጭንቅላቱን አደነዘዘው። አንድ ኤርትራዊ የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪ የነበር እንዳጨወተኝ በአሸናፊነት ወደ አማራው ግዛት ሲመጡ ህዝቡ ያለ የሌለውን በመስጠት ይንከባከባቸው ነበር። ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ ይሉት የነበረው ሜዳ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ አማራው ጭራቅ እየተባለ ነበር የሚነገረን ፤ እዚያ ስንደርሰ ግን በጭራቅ ፈንታ ርህሩህ ህዝብ እንጂ አንድም ጭራቅ አላየንም እያሉ እንደተናገሩ ከሌላው ኤርትራዊ ጓደኛው ጋር ሆኖ አጫውቶኛል። እንግዲህ በዚህ መልክ ነው ትግሉ ሲካሄድና ብዙ ወጣት ሲወናበድ የከረመው።

በዚህ የጥላቻ የትግል ዘዴ የኤርትራ ነፃ አውጭ ድርጅት እንቅስቃሴውን የማፊያ ባህርይ ሰጥቶታል። በአንድ በኩል በሃገር ቤት ውስጥ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ሲሰማራና

በጨርቅና በቆርቆር ሲነግድ ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ልዩ ልዩ መታወቂያዎችን ፎርጅ በማድረግ ብዙ ወጣት ኤርትራውያንን ውንብድና አስተምሯል። ነፃ ከወጡ በኋላም በዚህ ውንብድና ሙያ በመሰማራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢኮኖሚውን አሳድጋለሁ ፣ እንደ ሲንጋፖር እንሆናለን እያለ ያልፎከሩትን ያህል ይህ የማይደረስ ህልም እየሆነባቸው መጥተዋል። ዛሬ ሁለት ሶስተኛው የኤርትራ ህዝብ በዕርዳታ የሚኖርና የሚማቅቅ ህዝብ ሆኗል። በታሪክ ውስጥ በእንደዚህ ዐይነት የውንብድና ሙያ ተሰማርቶና በጥላቻ መንፈስ ተወጥሮ ዕድገትንና ዕውነተኛ ነፃነትን ለህዝቦቹ ያመጣ በፍጹም ታይቶ አይታወቅም። ከዚህ ባሻገር በመጠኑም ቢሆን ህዝቡ ነፃነት እስካላገኘ ድረስና በስለላ ሰዎች በየጊዜው ትክክል የሚደረግበት እስከሆነ ድረስ የአሁኑ የኤርትራ አገዛዝ እንደሚለው ኢኮኖሚው የተጠበቀውን የማቴሪያል ዕድገት ሊያሳይ በፍጹም አይችልም። ባጭሩ የኤርትራ አገዛዝ መንፈሳዊ ተሀድሶ እስካላደረገ ድረስና ከዚህ የጠብ ጫሪ ፖለሲ እስካልተላቀቀ ድረስ የኤርትራ ህዝቦች የሚመኙትን የኑሮ መሻሻል ሊቀዳጁ አይችሉም። ይህ ዐይነቱ የጥፋትና ከጎረቤት አገሮች ሃገሮች ጋር የመናደፍ ፖለቲካ ሌሎችም የብሄረሰብ ንቅናቄዎች ትምህርት ሊሆን ይችላል። ከዚህ ስህተት መማር አለባቸው። እንደ ሰው ራሳቸውን መጠየቅ መቻል አለባቸው። ችግርን በውይይት እንጂ እልክ በሚያስጨርስ የጦር እንቅስቃሴ እንፈታለን ማለት ሊወጡት የማይችሉት ማጥ ውስጥ ነው የሚገቡት። ስለዚህም የችግሩን ምንጭና ዘላቂ መፍትሄ ለመፈለግ ከውሸት ቅስቀሳ መላቀቅ አለባቸው።ለስልጣኔ የሚያበጀውን መንገድ መፈለግ አለባቸው።

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው አጠቃላዩን የህብረተሰብአችንን ችግር ማየት የምንችለው በፍልስፍና መነጽር ነው። የየብሄረ-ሰቦችም ችግር በዚህ መልክ መተንተንና ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት እንዲችል ሁላችንም ከግብዝነት ይልቅ ወደ ሳይንሳዊ ውይይት ማምራት መቻል አለብን። ፕላቶን እንዳለው ጭንቅላታችንን ወደ ውስጥ ለማንበብ መቻል አለብን።

## <u>የተማሪው እንቅስቃሴ አስተዋፅኦና ችግር</u>

ቀደም ብዬ ለማሰየት እንደሞከርኩት የተማሪውን እንቅስቃሴ ሚናና ስህተት በአንዳንድ ቦታዎችም ወንጀል መፈጸም ከጠቅላለው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አወቃቀር ነጥሎ ማየት በፍጹም አይቻልም። በመሰረቱ ኢትዮጵያ ወስጥ የደረሰውን መጥፎ ድርጊት በሙሉ የተማሪው ማህብር ማርክሲዝምን ስለተቀበለ ነው ብሎ መደምደምና የሚያሳስት ክስ ውስጥ መውደቅ የለብንም። መነሳት ያለበት ጥያቄ የተማሪው እንቅስቃሴ ለምን ይህንን መንገድ እንዲከተል ተገደደ ነው? ሌላ አማራጭ አልነበረም ወይ? ብሎ ጥያቄ ማቅረብ ተገቢ ይመስለኛል። በ1950ዎቹ ሆን ተብሎ የአሜሪካን ካፒታሊዝም በሶስተኛው ዓለም ሃገሮችም እየተስፋፋ ሲመጣ ከሱ ጋር የሱ የተበላሸና የተኮላሸ የትምህርት ስርዓት እየተስፋፋ መጣ። የትምህርት ስርዓቱ የየሃገሩን የዕድገት ሁኔታና የዕድገት ማነቆ ችግር ያካተተና የጭንቅላት ተሃድሶን በሚያመጣ መልክ መዘጋጀት ሲገባው የወጣቱን አስተሳሰብ የሚያኮላሽና የአሜሪካን ተገዢ የሚያደርግ እንዲሆን ሆነ። በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጭቆና ሲጠናከርና ዕድገቱም የተጠበቀውን ውጤት ማምጣት ሳይችል ትንሽ የተገለጸለት ራሱን ከማርክሲዝም ጋር ያገናኛል። ለህብረተሰብአችን ችግር ዋናው መፍትሄ የማርክስ ቲዎሪ መሆኑን ይቀበላል። እዚህ ላይ የተማሪውን እንቅስቃሴ ለሁለት ከፍሎ ማየት ያስፈልጋል። የሃገር ቤቱ ውስጥና የውጭው ሃገር። በውጭ ሃገር ደግሞ የአሜሪካውና የምዕራብ አውሮፓ። የታሪክ ግዴታ ሁኖ ወደ ምዕራብ አውሮፓ የመጣው ቀስ በቀሰ እያለ የተሻለ አመለካከት እየያዘና በአስተሳሰብ አድማሱም እየሰፋ ይመጣል። ከወዝአደሩ እንቅስቃሴም ጋር በመተዋወቅና በመካፈል ስለ አወቅሮፓ ህብረተሰብ ዕድገት የተሻለ ግንዛቤ ይይዛል። ይኸኛው በአመለካከቱ የበለጠ ምሁራዊና ራሱን በተሻለ መልክ ከማርክሲዝም ጋር ያስተዋወቀ ነበር ብሎ ዛሬ አፍን ሞልቶ መናገር ይችላል። ሃገር ቤት ውስጥም ሆነ አሜሪካን ያለው የተወሰነው ደግሞ በአስተሳሰቡ ለየት ያለ ፣ በተለይም ሃገር ቤት ያለው ባለው የማቴሪያልም ሆነ የማሰብ ኃይል ድክመት እንዲሁም ደግሞ የሊትሬቸር እጥረት የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ዕድገት በሰፊው ሊመለከት የቻለ አለነበረም። የሃገር ቤቱ የተማሪ እንቅስቃሴ የበለጠ ራዲካል እየሆነና በጥቂት ግንባርቀደም ነን በሚሉ እየተመራ በመምጣት ውጭ ካለው የተማሪ እንቅስቃሴ ጋር በፍጹም ሊጣጣም የማይችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። የሌላውን አስተሳሰብ የማይቀበል ፣ ለማዳመጥና ለመማር ጊዜ የማይሰጥ የተቻኮለ እንቅስቃሴ እየሆነ ይመጣል። ይህ ደግሞ የሚገርም አይደለም። አፄ ኃይለስላሴ ለምሳሌ ጥሩ ምክር የሚሰሙ አልነበሩም። የእነ አቶ ከበደ ሚካኤልን ሃገርን የማሰልጠን ፍላጎት በጆሮአቸው ውስጥ የሚያሰገቡና ለስልጣኔ ሽንጣቸውን ገትረው

የቆሙ አልነበሩም። በመሆኑም እንደዚህ ዐይነቱ ያለመደማመጥ ባህል ፣ እኔ ብቻ የምለው ነው ትክክል ብሎ በራስ ፍላጎት መጋለብ ፣ የህብረተሰቡን ዕድገት በቀጡ አለማጤን ወደ ተማሪው እንቅስቃሴም መዛመቱ የሚገርም አይደለም። ጥያቄው ማርክሲዝምን የመከተልና ያለመከትል ሳይሆን በጊዜው የተወሰነው የተማሪው እንቅስቃሴ ክፍል ማንም ጤናማ ሰው ማድረግ ያለበትን የነገሮችን ሂዴት በቅጡ የመመልከትና ሚዛናዊ ፍርድ የመስጠት ችሎታን አላሳየም። የኢትየጵያ አብዮት ከማንም ቁጥጥር ውጭ ሳይተሳብ ሲፈነዳ ሁኔታውን በቁጥጥር ስር የሚያውልና የትግሉን አቅጣጫ የሚያሲዝ ኃይል በፍጹም ብቅ ሊል አልቻለም። አፄ ኃይለስላሴ አፍነው የያዙት ህብረተሰብና የተከተሉት ዕድገት አቅጣጫ አንድ ምራቅ የዋጠና የተደላደለ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ እንዲል አላስቻለውም። የኢትየጵያ ህዝቦች ዕድልና የሃገሪቱ የወደፊት ዕድል በተማሪው እንቅስቃሴ እንዲወሰን ተገደደ።

ቀስ በቀስ ወታደሩ ስልጣን ሲጨብጥና ውስጥ ለውስጥ ሲታመስ የከረመውን የህብረተሰብ ችግርና ጥያቄ በመሬት አዋጁ አማካይነት ለመፍታት እርምጃዎች ሲወሰዱ የተወሰነው የተማሪ እንቅስቃሴ ክፍል ይህንን እንደ አንድ እርምጃ መደገፍ እንዳለበት አድረጎ አልተመለከተውም። ከዚህ ጋር ተያይዘው የታወጁት አዋጆች በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ከመታገል ይልቅ ሁሉም ታጋይ በመሆን በህብረተሰብ ውስጥ ትርምስ ሊፈጠር ቻለ። ሁሉም ፊናውን የሚለይበትን መንገድ ወደ ማዘጋጀት አመራ። ከዚህም ከዚያም የሚወረወሩት መፈክሮች የህዝቡን ጭንቅላት በማደስ ፈንታ ለጦርነት የሚጋብዙት የሚመስሉ ነበር። አንዱ በሌላው ላይ የሚነሳና ፣ አንዱ ሌላውን እየፈራ የሚኖርበት ጊዜ እየሆነ መጣ። ለጥቂት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በፍጹም ዲሞክራሲያዊ ውይይት ለማድረግ የሚቻልና ሃሳብን በማንሸራሸር በጥሞና ለማስረዳትና ለማሰመንና ለማመን የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጠረ። በአብዮቱ ወቅት በህብረተሰቡ ወስጥ ከሜታፊዚክሳዊ አንፃር መፈታት ያልቻሉ የጭንቅላት ችግሮች አፍጠው አግጠው በመምጣት ሁሉም በጎሪጥ የሚተያይበት ሁኔታ ተፈጠረ። ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ባልዳበረበትና የከበርቴው ራሽናሊዝም ባልተስፋፋበት ሃገር ደግሞ ከዚህም ከዚያም የመጣ ብሄረ-ሰብ ፣ እዚህም እዚያም በተለያየ መልክ የሚታየው ህብረተሰብአዊ ቅራኔ ጉልህ እየሆነና ህብረተሰቡን እያዳረሰ መጣ። በተለይም ሙልጭልጩ የከተማ ንዑስ ከበርቴ ራሱን የሚያዘጋጅበትና በጭንቅላት ውስጥ ያለውን የተተራመሰ ቅራኔ ወደ አመጽ የሚቀይርበት ሁኔታ ተመቻቸለት። ቂም በቀል መወጣትና መፋለም ለጊዜውም ቢሆን የህብረተሰቡ ኖርም በመሆን የህበረተሰቡ የማቴሪያልና የመንፈስ መሻሻል ማደግ የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። በእውነቱ በማርክሲዝም ስም የገባው የቅስቀሳ ዘዴ የህዝቡን የማሰብ ኃይል ሁኔታ ይህንን ያህልም አላሻሻለውም። ዕውነተኛ ግለሰብአዊ ነፃነትና ራስን ማወቅ መሰረታዊ የሆኑ የህብረተሰቡ የዕድገት መመሪያዎች ሊሆኑ አልቻሉም። በየፊናውና በየድርጀቱ አካባቢ የሚታገለው ሁሉ ትግሉን በራሱ ድርጅ መነፅር የሚመለከት እንጂ የሌላወንም የትንተና ዘዴ የራሱ የትግል ዘዴ ውስጥ ሊያካትት የሚችል አልነበረም። ሁሉም የየራሱን ዕውነት ይዞ የሚጓዝ እንጂ ሳይንሳዊ የህብረተሰብ መታገያ መመዘኛ በመፈለግ ወደ አንድ አቅጣጫ ሊመጣ የሚችል አልነበረም። ይህ በተለይም የተወሰነው የንዑስ ከበርቴው ክፍል ተደናብሮ ሌላውንም ማደናበር በተለይም ጡብመንጃ የያዘውን ደርግ አስቆጣው። ሃገሪቱ ወደ ማያስፈልግ ርስ በርስ ጦርነት አውድማ አመራች። በዚህ ላይ ከዚህም ከዚያም በነፃነት ስም የተቀጣጠለው እሳትና ውስጥ ለውስጥ የውጭ ኃይሎች ጣልቃ መግባት ሁኔታውን አባባሰው። ተማርኩ የሚለው ግን ይህንን የውጭ ኃይሎችን ሴራና የብሄረ-ሰቦችን እንቅስቃሴ አደጋ ሊታየው አልቻለም። በራሱ ቅዠት ውስጥ የሚሽከረከር ስለነበር በህዝባችንና በሃገራችን ላይ የሚያንዣብበውን አደጋ ጠጋ ብሎ መመልከትና መመርመር አልቻለም። በሁኔታው በመሳከሩና ወደ ድልም ያመራ ይመስለው ስለነበር ተፈጥሮአዊው አርቆ የማሰብ ኃይሉ እየታፈነና ወንድሙንና እህቱን እየቀነጠሰ አጉል ጀግንነት ተሰማው። ይህ አጉል ግብግብ አንድ የተማረና በጊዜው ለዕድገት ሊሰለፍ የሚችልን ኃይል እንዳለ እንዲቀነጠስ አደረገ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሃገራችን በልዩ ልዩ መስክ ልታድግና እንደ ሃገር ልትጠነክር የምትችልበት ሁኔታ እየተቀጨና ደብዛው እየጠፋ መጣ። ጥሩ የምሁር እንቅሳቀሴ ባህል እንዳይዳብር አገደ። በአንፃሩ ሰርዓት የሌለው ፣ ለሆዱ ብቻ ያደረ የካድሬ ባህል እንዲስፋፋ አደረገ። አገዛዙ የምሁሩን እንቅስቃሴ ሁኔታ በመመልከትና አሸንፌያለሁ ብሎ በመገመቱ ፣ በአንድ በኩል የቢሮክራሲው ጉያ ስር እየገባ ሲመጣ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ጥራዝ ነጠቅ የካድሬ ባህል በማስፋፋት የዕድገትን አቅጣጫ ለማሳሳት በቃ። ይህ በራሱና በየጊዜው የሚወሰዱት የተሳሳቱ እርምጃዎችና ከዚህም ሆነ ከዚያኛው ርዕዮተ-ዓለም የማይዳበሉ እርምጃዎች አገዛዙን እየገዘገዙት መጡ። ጥንካሬን ከመስጠት ይልቅ መፈረካከስ አፋጠኑለት። ይህ ሁኔታ ለብሄረ-ሰቦች እንቅስቃሴና ለፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች መፈናፈኛ እየሰጠና ኃይላቸውን እያጠናከሩ ወደ መሀል ሃገር መገስገስ ቻሉ። በተለያዩ አጋጣሚዎችና በውጭ ኃይሎች በመታገዝ የዛሬው የኢህአዴግ አገዛዝ ስልጣን ሊይዝ ቻለ። በአሸናፊነት ወጣሁ ብሎ

*መዝናናት ጀመረ። አጀንዳውን ቀስ በቀስ ተግባራዊ እያደረገ መጣ። እጅግ ርስ በርስ በሚቃረኑ ፖሊሲዎች እየታገዘ የህብረተሰቡን የመፈረካከስ ሁኔታ እያፋጠነ መጣ።*

## ***<u>የዛሬው አገዛዝ ሁኔታ</u>***

*የዛሬው አገዛዝ የኢትየጵያ የተዘበራረቀ የኢኮኖሚና የህብረተሰብ አወቃቀር ውጤት ሲሆን ፣ በአስተሳሰቡ እጅግ ወደ ኋላ የቀረ ነው። የአገዛዙን አስተሳሰብ በአንድ ወጥ ቲዎሪ ለመግለጽ ያስቸግራል። ባጭሩ ማለት የሚቻለው ፣ ፊዩዳላዊ ተንኮልን ፣ የዝቀተተኛ ስሜትን ፣ የንዑስ ከበርቴውን አጉል ብልጣ ብልጥነትን ፣ የከተማ ልጆችን ሽወዳና ውሸት ከራሱ ጋር ያዋሃደ ነው። በዚህ ላይ ሚሊታሪያዊ ኃይል ሲታከልበት ራሱን ወደ ማንኛውም ጭካኔ እርምጃ ሊቀይር የሚችልና በተግባርም የታየ ነው። በመጀመሪያዎቹ ወቅት የደርግን ፋሺስታዊ ድርጊት አጋልጣለሁ ብሎ ይዝናና የነበረው ኢህአዴግ የሱን ቦታ በመውሰድ በአለፉት 17 ዓመታት ህብረተሰብአችን መቅመስ ያለበትን መራራ ነገር ሁሉ እንዲጋት አድርጓል። የዛሬ አስራስድስት ዐመት ኤህአዴግ የደርግን ጭካኔ ለማረጋገጥ በቪዲዮ የሚያሳው ፊልም ነበር። ይኸውም አንድ የደርግ የጸታ ሰው የሰራውን ወንጀል ኤህአዴግ ውጭ ሃገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ያሳያል። የጸጥታው ሰው በተማርኩት ሳይንስ እንደዚህ አደርግ ነበር እያለ በእስረኞች ላይ ይሰራ የነበረውን ወንጀል ይዘረዝር ነበር። የጭካኔ ሳይንስ ማለት ነው ግለሰቡ የተማረው። ይህንን ድርጊት ግን የኢህአዴግ የጸጥታ ሰዎች በሌላ መልክ እያደረጉ መጥተዋል። በሰው ጆሮ ስር ጥይት እያጮሁ ብዙ ሰው ራሱን እንዲስት አደርገዋል። የየግለሰቦችን ሀብት ለመዝረፍ መርዝ እስከማጠጣት ደርሰዋል። እንደዚህ ዐይነቱ ድርጊት በቤተክርስቲያንና እጅግ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ባለቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አካባቢ የተለመደ ቢሆንም ትንሽ የፖለቲካ ሀሁን የቀመሰ ሰው እንደዚህ በይፋ ማድረጉ እጅግ የሚያሳዝን ነው።*

*ከ17 ዐመት ድርጊቱ መረዳት የምንችለው ፣ ኢትዮጵያን በዚህ መልክ ለመግዛት ከመጀመሪያውኑ በጭንቅላቱ የቋጠረው አጀንዳ ነበር ብሎ መናገር ይቻላል። 1ኛ) የብሄረ-ሰብን ጥያቄ ጎላ አድርጎ በማስቀመጥ በነፃነት ስም የክልልን ፖለቲካ ተግባራዊ አደረገ። በዚህም መልክ እያንዳንድ ብሄረ-ሰብ የማሰብ አድማሱ ብሄራዊ ባህርይ አይኖረውም ማለት ነው። ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ የራሱን ብሄረ-ሰብ እያጎላ በማንሳት ጠባብ አመለካከትን ያጠነክራል። ይህ ሁኔታ በራሱ አንዱ ብሄረ-ሰብ በሌላው ላይ ዕምነት እያጣና በጋራ ሊሰሩ የሚችሉት ነገሮች እየታገደ ዕድገትን ከማየት ይልቅ እዚያው በክልላቸው ቀጭጨው እንዲቀሩ የሚያደርግ ነው። በዚህ መልክ በሄራዊ ኢኮኖሚ ማሳደግ አይቻልም። በልዩ ልዩ መልክ የሚደረግ መደጋገፍና የንግድ ልውውጥ እንደልብ ሊካሄድ አይችልም። በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሶስትና አራት ዐመታት ይህ ሁኔታ ነው የታየው። 2ኛ) የሀይማኖትን ጥያቄ የመከፋፈያ መሳሪያ በማድረግ ፣ በአንድ በኩል በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ውስጥ ክፍፍል እንዲኖር ማደረግና ግጭቱ ወደ ውጭ ወጥቶ በኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ድረስ እንዲዳረስ ማድረግ። ህዝቡ በሀይማኖት ሰበብ በሚነሳ ግጭት ውጥረት ውስጥ እንዲወድቅ ስነስርዓትንና ህግን ያልተከተለ የቤተክርስቲያንና የመስጊድ ስራ ሲከናወን ዝም ብሎ ማየት። በተጨማሪም በኦርቶዶክስ ሀይማኖትና በፔንጤ ቆንጤ ሀይማኖት ተከታዮች ዘንድ ግጭት እንዲፈጠር የሃገሪቱን በር ልቅ ማደረግና የህብረተሰቡን መንፈስ መረበሽ። 3ኛ) በህብረተሰቡ ውስጥ ልቅ የሆነ የአኗኗር ስልት እንዲስፋፋ ማድረግ። በተለይም የወጣቱን መንፈስ ለማዳከም የመንፈስን ጥንካሬ ሳይሆን ማንነቱን እንዲረሳ የማያደርጉ የቪዲዮ ፊልሞች ከውጭ ሃገር በብዛት እንዲገቡ ማድረግ።4ኛ) ጭንቅላትን የሚያደነዝዙ እንደ ዕጽና ጨአት ሲስፋፋ ዝም ብሎ መመልከት። 5ኛ) በተለይም ወጣት ሴቶች ለአደጋ ሲጋለጡ ዝም ብሎ ማየት። የሃገሪቱን በር ልቅ በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደ ኤይድስ የመሳሰሉት በሽታዎች በወጣቱ ዘንድ እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታዎች መፍጠር። 6ኛ) ተግባራዊ ያደረገው የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ የህብረተሰቡን የማምረት ኃይል ከማዳከሙም በላይ አዲስ ፈጣሪ ያልሆነ የሀብታም ክፍል እንዲከሰት በማድረግ በአንድ በኩል ያልተስተካከለ ዕድገት እንዲፈጠር ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሀብታምና በደሀ መሀከል ያለው ልዩነት እንዲሰፋ ማድረግ። እነዚህ የተዘረዘሩት ነጥቦች አገዛዙ ምን ያህል ጭንቅላቱ እንደተሸፈነና ሃገሪቱን ወዴት እንደሚያመራ ለመገንዘብ የማይችል መሆኑን ነው የሚያረጋግጠው።*

*ይህ አገዛዝ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ብቻውን ቆሞ የሚጓዝ አልነበረም። እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያዊ ነኝ እያለ የግንባር ቀደምትነቱን ሚና እጫወታለሁ እያለ እዚህና እዚያ የሚረ ፗረጠው ኃይል አልዋጥለት ያለው የኢህአዴግና የውጭ ኃይሎች*

በተለይም የአሜሪካንና የኢንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ያልተቀደሰ ጋብቻ ነው። እጅግ በተሳሳተ የትግል ስልት የሚታገለው ተቃዋሚ ነኝ የሚለው የተወሰነው ኃይል ይህንን ሀቅ በፍጹም ሊገነዘብ አልቻለም። የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያ ብትፈረካከስ ምን ያገኛሉ እያለ ከታሪክ ጋር ያልተገናዘበ ወሬ በማውራት ለዕወነተኛ ነፃነት የሚደረገውን ትግል እያሳሳተ ነው። ባገኘው ዝና እየተዝናና በራሱ ዓለም ውስጥ በመኖርና በመሽከርከር እንዲሁም በተወሰነ ርዕየተ-ዓለም በመጠመድ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን እያሳሰተ ነው። መታየት የሚገባቸውን ነገሮችና ለትግሉ ሊያግዙ የሚችሉ የቲዎሪና የሳይንስ መመሪያዎችን ወዲያ በማለት የትግሉን አቅጣቻ እያሳተ ነው። ያም ሆነ ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ህዝቦች እሮሮና በጫንቃቸው ላይ የተጫነው ችግር የአገዛዙና የወጭ ኃይሎች ጥምር ሴራ ነው። ከዚህ ውጭ ማየት ኢትዮጵያ ውስጥ ዕውነተኛ ስልጣኔ እንዳይመጣና ሃገራችን ብሄራዊ ነፃነቷን ጠብቃና አስከብራ እንዳትኖር ከሚሸረበው ዓለም ዓለም አቀፋዊ ሴራ ተነጥሎ መታየት አይችልም።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አገዛዙ በዚህ የጥፋት ዘመቻው ለምን ዐይኑን ጨፍኖ ይጓዛል ? ለምን ጥፋቱ አይታየውም ? ምንስ ጥቅም ያገኛል ? እንደዚህ ዐይነት የጭንቅላት መታወር በታሪክ ውስጥ የታየ ነው። በተለይም ወደ ኋላ ከቀረ ህብረተሰብ የሚፈልቁ አገዛዞች ህብረተሰቡን የሚያስተዳድሩበት ሳይንሳዊና የቲዎሪ መሳሪያ ስለሌላቸው አንድ ህብረተሰብ በዘፈቀደ የሚኖር ይመስላቸዋል። ስርዓትና ጥበባዊ የተሞላበት ኑሮ በፍጹም አይታያቸውም። ባገኙት ኃይልና ባካበቱት ሀብት በመታወር አንድ ህዝብ እንደ እንሳሳ የሚኖር ይመስላቸዋል። ፍላጎት ያለው ፣ ፍቅርና የተደላደለ ኑሮ የሚመኝ አይመስላቸውም። ይህ የተሳሳተ ርዕዮተ-ዓለምና ጠባብ አስተሳሰብ ሲታከልበት የባሰውኑ አረመኔ እየሆኑ ይሄዳሉ። ከአንድ ጥፋት ወደ ሌላ እያመሩ የሚሰሩት መጥፎ ድርጊት ሁሉ ትክክል ይመስላቸዋል። ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ማየት ይሳናቸዋል። በታሪክ ውስጥ የተነሱትና የወደቁት ኢምፓየሮች ታሪክ ይህንን ነው የሚያረጋግጠው ። ናፖሊዎን አውሮፓን የሚቆጣጠር መስሎት ነበር። ሂትለርም ሌላውን አዳክሞና አጥፍቶ ጀርመን በሁሉም አገር ትኑር እያለ በመዝመት በጥላቻና በዝቅተኛ ስሜት በመመራት ወደ ሃምሳ ሚሊዮን ለሚጠጋ የአውሮፓ ህዝብ ዕልቂት ምክንያት ሆኗል። በዚህ የጥፋት ድርጊቱ ፈላስፋዎች ፣ የሳይንስ ምሁሮችና እንዲሁም የድራማ ሰዎች በማበር እነሱም በሱ መፍክር ታውረዋል። ምን እንደሚያደርጉ አያውቁም ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን የመስፋፋት ጉዳይ ሳይሆን እዚያው በዚያው ሃገርን ማዳከምና በራስ ድርጊት እየተዝናኑ ማበጥና በአየር ላይ መንሳፈፍ ነው። ይህ ድርጊቱ እየተለመደ ሲመጣ ርካታን እየሰጠው እየተደሰተ በመዝናናት ላይ ይገኛል። ይህ ደግሞ በሳይኮሎጂ የተደገፈ ነው። በሰው ስቃይ የሚደሰቱ አሉ። ሲገድሉ የሚረኩ አሉ። አንዳንዶችም ሲገረፉና ሲደበደቡ ስሜታቸው የሚቀሰቀስ አለ። ይህ ከጥቂት ሰዎች ጋር ያለ በሽታ ነው። አሁንም ወደ ሃገራችን ስንመጣ ፊዩዳላዊ አስተሳሰብ እጅግ ስር የሰደደ ስለሆነ እስከዛሬ ድረስ ሲያሰቃየን ይኖራል። የዚህ ተጠናክሮ መኖር ከቦታ ወደ ቦታና ከህብረተሰብ ክፍል ወደ ህብረተሰብ ክፍል ይለያያል። እንደ ፊዩዳሉ አገዛዝና ባህል መጠናከርና መላላት እንዲሁም ደግሞ እንደቤተሰብ ሁኔታ የተከታዩም ትውልድ አስተሳሰብ መበላሸትና ቀና መሆን በዚህ የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ ሊገመትና ሊተነተን የሚችል ነው። ሌሎች በደንብ ሳይጠኑ ከውጭ የመጡ ባህሎችና አመለካከቶች  ሁኔታውን ያባብሱታል። ጭንቅላትን ከማደስ ይልቅ እንዲሸፈን በማድረግ የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ታሪካዊ ተልዕኮውን እንዳይወጣ ይታገዳል። ድርጊቱ ሁሉ ጥፋት ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ አይ ህብረተሰቡ ከአገዛዙ ጋር እንዳለ ይወድማል ወይም ይበታተናል ካሊያ ደግሞ በከፍተኛ ንቃተ-ህሊና በሚታገዝ ኃይል የሚተካ ይሆናል። በዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ግን የመጀመሪያው የሚፈጥን ይመስላል። የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድል የጨለመ ይመስላል።

## <u>የተቃዋሚው ችግርና ሚና</u>

የተቃዋሚው ኃይል ችግር ከላይ የተዘረዘረውን ሁኔታ በፍልስፍና መነጽር ለማየት ያለመቻል ነው። ዲሞክራሲና ሊበራሊዝም በሚሉ ቀላል መፈክሮች ግን ደግሞ በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆን በማይችሉ ጽንሰ-ሃሳቦች ዙሪያ እየተሽከረከረ የነገሮችን ሂደት ሊከታተል አልቻለም። አብዛኛው ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ኃይል አብዮቱ ከከሸፈ በኋላ ራሱን ማደስ የሚገባውን ርምጃ ሊወስድ አልቻለም። አብዛኛው በድሮው አስተሳሰቡ ተወጥሮ ወደ ፍልስፍናና ወደ ሌሎች ጭንቅላትን ወደ ሚያድሱ ነገሮች ለማምራት ዕድል ባለማግኘቱ

ሁኔታው ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ እየሆነበት መጥቷል። አንዳንዱ በድርጀቱ አማካይነት ብዙ ነገሮች መስራት ሲችልና ራሱንም መጠየቅ ሲገባው በተሳሳተ ህልም ውስጥ በመውደቅ ማደረግ የሚገባውን ሳያደርግ ቀረ ። ሌላው ደግሞ ብቻውን ትግል የሚያካሂድ እየመሰለው እዚህና እዚያ እየተሸሎከለከ ሌሎች የሚያደርጉትን ትግል ወደ ማጨናገፍ አመራ። በዚህ የተተራመሰ ሁኔታ ውስጥ ኢትዮጵያን እናድናለን እያሉ እዚህና እዚያ ውርውር የሚሉ ደርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች በላፈው 17 ዓመት ብቅ ብለዋል። አብዛኛዎቹ እዚያው በዚያው የሚሽከረከሩ(recycle)ፖለቲከኞች ሲሆኑ ከሳይንስ አንፃር ትግሉን የመምራት ብቃት አላሳዩም። ትግላቸው ፕሮግራም ከማውጣትና ከድህረ-ገጽ ዜና ሊያልፍ የቻለ አይደለም።

ከምርጫ 1997 ዓ.ም ወዲህ ለአጭር ጊዜ የተፈጠረው መሰባሰብ ደስ ቢልም የምርጫው ውጤት ሲኮላሽ ሁሉም መደናበር ጀመረ። በአሸዋ ላይ እንደተገነባ ቤት የሚፎክረው ሁሉ መበታተን ጀመረ። ሌላው ደግሞ ጎራ ፈጥሮ ርስበርሱ መበላላት ጀመረ። ይህ ጉዳይ ለጊዜው ለአገዛዙ እስትንፋስ ሰጠው። የዚህ ሁሉ ችግር ምንድነው ? አብዛኛው አስተሳሰብን በሚሰበስብ ፍልስፍና የሚመራ አይደለም። የራሱ የሆነ የኑሮ ፍልስፍና የለውም። የተወሰኑ መሪ ነን የሚሉ ሰዎች ሲመጡ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ እነሱ ወደ መሩት የሚመራ ነው። ድርጊታቸውን ፣ የሚመሩበትን ፍልስፍናና ፖሊሲ ከራሱ ፍልስፍና ጋር እያገናዘበ ሊመረምርና ሂደታቸውን ሊቆጣጠር የሚችል አይደለም። በስማቸው የሚዝናና ያለደረጉትን አደረጉ ብሎ የሚሸመጥጥና በራሱ ላይ ዕምነት የሌለው ነው። አንዳንዱ “የቸገረው ርጉዝ ያገባል ፣ እሷ ስትሞት ገደል ይገባል” እንደሚሉት ዐይነት እነሱ ሲደናበሩ አብሮ የሚደናበር ነው። ሌላው ደግሞ ዛሬ አቶ እከሌን ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዶክተር እክሌን በመደገፍ አንዱን ሲያወድስና ሌላውን ሲሰድብ የሚውል ነው። ባጭሩ ግራ በተጋባ ዐለም ውስጥ የሚኖርና የሚያደርገውን የሚያውቅ አይደለም። *ከዚህ በተረፈ ሁላችንም ለምን ዐይነት ህብረተሰብ እንደምንታገል በቅጡ የገባን አይመስለኝም። ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ያጠናነውና በጭንቅላታችን ውስጥ የቀረጽነው ይህንን ለሚመስል ዐይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገለው ብለን ከሰውነታችን ጋር ያዋሀድነው የህብረተሰብ ርዕይ የለም። እንደዚህ ዐይነት ትልም በጭንቅላትቻን ውስጥ ስለሌለ የችግሩን ምንጭ ልንረዳ አልቻልንም። የምንፈለገውን ካላወቅን ደግሞ እንዴት አድረገን ደረጃ በደረጃ መታገል እንዳለብንና ችግሮችንስ በምን መልክ መወጣት እንዳለብን ልንገነዘብ አንችልም።* ባጭሩ ዝም ብለን ነው የምንደናበረው ማለት ነው። መሪ ነን የሚሉት ደግሞ በሳይንሱ የህብረተሰብአችንን ችግር በመተንተንና መፍትሄ በመስጠት ካለንበት ማጥ ውስጥ ለመውጣት እንድንችል ሲጠቁሙን አይታይም። በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ በጥናት ላይ የተመረኮዘ ውይይት ሲካሄድ አይታይም። እታገላለሁ የሚለው ለስሙ የሚታገል እንጂ ኃላፊነት አለብኝ ብሎ በአንድ ነገር ላይ በማትኮር ጥናት አቅርቦ ሌላውን ሲያሰተምር በፍጹም አይታይም። አብዛኛው በፕሮግራም ብቻ ሃገር የሚገነባ የሚመስለው አለ። ለአንድ ህብረተሰብ እንደ ህብረተሰብ እንዲኖር ከተፈለገና ጠንካራ ሃገር እንዲገነባ ምኞት ካለ ልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች እንደሚያሰፈልጉና እነዚህም በየጊዜው መሻሻልና በሰፊው ለተራውም ህዝብ መሰራጨትና ለህዝቡም መመሪያ መሆን እንዳለባቸው ግንዛቤ የለም። ብዙዎቻችን ባለንበት አካባቢ እዚህና እዚያ ተበታትነን ስለምንኖር በምንኖርበት ሃገር ምን እንደሚሰራና ከነሱስ ብዙ ቁም ነገሮች መማር እንዳለበን ቁም ነገር ውስጥ የገባ ነገር የለም። ባለንበት ሃገር ከህብረተሰቡ ጋር ያለን ግኑኝነት የላላ ብቻ ሳይሆን ራሳችን በራሳችን ፍላጎት በመቅረብና ወዳጅ በማፍራት ከነሱ ለመማር ዝግጁ አይደለንም። ብዙዎቻችን በራሳችን ክልል ውስጥ ብቻ ስለምንሽከረከር በራሳችን ላይ ዕምነት እያጣን ነው። በዚህም ምክንያት በብዙ ቦታዎች የኋሊት ጉዞ ይታያል። እየተወሳሰበ የመጣውን ዓለም ለመረዳት የማንችልና ራሳችንንም ለመለወጥ ዝግጁ አይደለንም። በመሆኑም ራሳችንንም ሆነ መሪዎች ነን የሚሉትን ለማወቅ የተቸገርነበት ሁኔታ ውስጥ ወድቀናል። ከዚህ ችግር ለመውጣት በአንድ በኩል በራሳችን ላይ ለውጥ ማምጣት አለብን ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መሪ ነን የሚሉትን ምንነት ለማወቅ ከፍተኛ ትግል ማድረግ አለብን። *የአሰተሳሰብና የአሰራር ስልት ለውጥ በማይታይበት ሃገር ውስጥ ምንም ውጤት ማምጣት አይቻለም።* ከዚህ ባሻገር ፖለቲካ የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ በደንብ ማብራራትና መረዳት ያስፈልጋል። ፖለቲካ ጥበብ የተሞላበት የአስተዳደር ስልት ወይስ የቂም በቀል መወጫ ዘዴ። በሁለቱ መሀከል ያለውን ልዩነት በቅጡ መገንዘብ እጅግ ሰፈልጋል። በተጨማሪ አቅማችንን ማወቅ አለብን። ፖለቲካ ጀብኝነትን ሳይሆን የጭንቅላት ስራን የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን የቱን ያህል ጊዜያችንን ልንሰዋ እንችላለን የሚለውን ማጤን አለብን። እንደሚታወቀው ፖለቲካ ለሁሉም የሚሆን አይደለም። የፖለቲካ ትግል እጅግ የተወሳሰበ እንደመሆኑ መጠን ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው ሊረዱት የሚችሉት። ስለዚህ ሁሉም በማይችለውና በቀላሉ በማይረዳው ውስጥ እየገባ ከማተረማመስ ይልቅ በሰለጠነው ሙያ ቢገፋበት ለራሱም ሆነ ለሃገሩ ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል። የዛሬውም ዋናው ቁም ነገር ሁሉም በሚችልበት አስተዋፅኦ ማደረግ ነው። ፊዚክስ ያጠናው በፊዚክስ ሙያው ቢገፋበትና ወደ አማርኛ እየተረጎመ ወጣቱን

ሊያስተምር ቢችል ትልቅ ፖለቲካ ሰራ ማለት ነው። ሌሎችም በየሙያዎቻቸው እንደዚህ ጥረት ቢያደርጉና ሃሳብ ለሃሳብ ቢለዋወጡ ለትግሉ የበለጠ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ። የዛሬውንም ሁኔታ መቆጣጠር የምንችለው አገዛዙን ጠለቅ ባለ ዕውቀት ስንጋፈጠውና በሞራልም ከሱ የተሻልን ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው። ፖለቲካ ከፊዩዳላዊ ባህርዩ ካልተላቀቀ ጭንቅላት ስለሚጋረድ የመጨረሻ መጨረሻ ወደ ጥፋት ነው የሚየመራው። አሁንም ቢሆን ለዚህ ሁሉ የጭንቅላት ትግልና ራስን ነጻ ለማውጣት የሚደረገው ትግል ቅድሚያ መሰጠት አለበት። ይህ ብቻ ሲሆን የራስን ምንነት አውቆ ታሪክን መስራት ይቻላል።


**ፈቃዱ በቀለ**

e-Mail: fekadubekele@gmx.de


## የተጠቀምኩባቸው መጻህፍት


1. Callaghan, William. An Outline Of Plato`s Republic and Dialogues. USA,1938
2. Cusa, Nicholaus. On Learned Ignorance. Hamburg, 1970.
3. Fromm, Erich. Analytical Social Psychology and Social Theory. Frankfurt aM, 1982.
4. Hutcheson, Francis. An Inquiry into the Original of Our Ideas of Beauty and Virtue. New York, 1971.
5. Kohanski, Alexander. The Greek Mode of Thought in Western Philospthy. London and Toronto, 1984.
6. Schiller, Friedrich. Theoretical Writings. Köln, 1999.